# “መስመር’ዩ ሓይልና”፡ የትግራይ ክልል መዝሙር ከማታገያነት እስከ ክልል መዝሙርነት

**መስፍን መሰለ**

**አኅጽሮተ ጽሑፍ**

“መስመር’ዩ ሓይልና” በሚል የሚታወቀው የትግራይ ክልል መዝሙር የተደረሰውና አገልግሎት መስጠት የጀመረው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የትጥቅ ትግል ያካኼድ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ ህወሓት ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንባር ፈጥሮ ሥልጣን ላይ የነበረውን የኢትዮጵያ መንግሥት በወታደራዊ ኃይል አሸንፎ ሥልጣን ከያዘ በኋላም መዝሙሩ አገልግሎት መስጠት ቀጠለ፡፡ በመጽሐፍ ታትሞም በክልሉ ትምህርት ቤቶች ጠዋት የክልሉ ሰንደቅ ላይ ሰንደቅ ዐላማ ሲሰቀል እንዲዘመር ተደረገ፡፡ መዝሙሩ ከማታገያነት እስከ ክልል መዝሙርነት ቢያገለግልም የተመራመሪዎችን ትኩረት አላገኘም፡፡ ይኽን ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበትም በመዝሙሩ ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖር ነው፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 የተደነገገው በመዝሙሩ መንጸባረቅ አለመንጸባረቁንና የመዝሙሩን መልእክት መመርመርና መተንተን ነው፡፡ የዚኽ ጥናት የመረጃ ምንጮች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት፣ የትግራይ ክልል ሕገ መንንግሥት፣ የክልሉ መዝሙር፣ የተለያዩ ዐዋጆች፣ ክልሉን የሚመራው የፖለቲካ ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም፣ የታሪክ ሰነዶች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና በራሪ ጽሑፎች ናቸው፡፡ በመዝሙሩ የተንጸባረቀው የተመረመረውና የተተነተነው የመዝሙሩን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግና ገላጪ የትንተና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 የተደነገገው በክልሉ መዝሙር አልተንጸባረቀም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ረጅም ታሪክ በህወሓት የትግል ታሪክ የተገደበ ነው፡፡ መዝሙሩ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለበት ሳይኾን ወጣቱን ለትግራይ ሕዝብ “ነጻነት” እንዲታገል የሚቀሰቅስ፣ የሚያነሣሣና ለመስዋዕትነት የሚያዘጋጅ ነው፡፡ የክልሉን ሥልጣን የያዘው መንግሥት መዝሙሩን እንዲዘመር የሚያደርገው ማንን ለመታገልና ሕዝቡን ከማን ነጻ ለማውጣት  አስቦ እንደኾነ ግልጽ አይደለም፡፡ ለክልሉ መዝሙር ያስፈልጋል ከተባለ የክልሉ ሕዝብ ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ አካል መኾን በትክክል የሚያንፀባርቅ፣ በሌሎች ክልሎች ከሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በእኩልነት መኖርን የሚያስተምርና ኢትዮጵያዊ ስሜትን የሚያጎለብት፣ የአጠቃቀም ሕግ ያለው  መኾን ይገባዋል፡፡

<u>ቁልፍ ቃላት</u>፡- [ሕገ መንግሥት፣ መዝሙር፣ የትግል ታሪክ፣ ብሩኅ ተስፋ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ አብሮ የመኖር እምነት፣ ትህነአድ/ተሓህት/ ሕወሓት]

## 1) መግቢያ

ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ. ም. "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት"ን በወታደራዊ ኀይል ከሥልጣን ወረደ፡፡ ሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት ያዋቀራቸው ክፍላተ ሀገርና ራስ ገዝ የአስተዳደር መዋቅሮች እንዲቀሩ ተደረገ፡፡ መንግሥትን ከሥልጣን ያስወገዱት "ልዩ ልዩ የብሔሮች ነፃነት ግንባሮችና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በአዲስ አበባ ከተማ ከሰኔ 24 ቀን እስከ ሰኔ 28 ቀን 1983 ዓ. ም. ድረስ የሰላምና የዲሞክራሲ ጉባኤ አድርገው የሽግግር መንግሥት አቋቋሙ" (አዋጅ ቁጥር 7/1984 መግቢያ)፡፡ በአዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 3 (1) በአብዛኛው ቋንቋን መሠረት በማድረግ ዐሥራ አራት ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳደሮች ተመሠረቱ፡፡ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳደሮቹ እያንዳንዳቸው የተጠሩት በቁጥር ነበር፡፡ በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮቹ የሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስም ተዘርዝሯል፡፡ በዚኹ መሠረትም ክልል አንድ ተብሎ በተጠራው ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር የሚገኙት ብሔር-ብሔረሰቦች ትግራይ፣ ሳሆና ኩናማ ናቸው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ክልል አንድ ተብሎ የነበረው ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የትግራይ ክልል ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ክልሉም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ አባል ክልሎች[1] አንዱ መኾኑ ተደንግጓል፡፡ በሽግግር መስተዳድሩ የክልል አንድ አባሎች ተብለው የተጠሩት ሳሆና ኩናማ ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይን ክልል ሕገ መንግሥት ለማጽደቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 39 ከትግራይ ብሔር እኩል የክልሉ ሥልጣን ባለቤቶች መኾናቸው ተደንግጓል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ረፐብሊክ (ኢፌዴሪ) መንግሥት ሕገ መንግሥት ክልሎች የየራሳቸውን የክልል መዝሙር የማውጣት ሥልጣን እንዳላቸው በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ኾኖም፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 1 "በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ መንግሥት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን ይሆናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይኽንን ሕገ መንግሥታዊ መብት መሠረት በማድረግ የትግራይ ክልል የራሱ ክልል መዝሙር እንደሚኖረውና መዝሙሩ[2] የሚያንፀባርቀውን በአንቀጽ 4 ደንግጓል፡፡

የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት መዝሙሩ እንዲያንፀባርቅ የተደነገገውን ማንፀባረቁን ወይም አለማንፀባረቁን እንዲኹም የመዝሙሩን መልእክት  መመርመርና መተንተን

---

[1]ተሻሽሎ በወጣው የትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 1 የክልሉ መጠሪያ "የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት"መኾኑን ይደነግጋል፡፡ ይኹን እንጂ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የትግራይ ክልል በሚል ይጠራል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ መሠረት የትግራይ ክልል ስያሜ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ክልል የሚል በመኾኑ በዚኽ ጥናት ክልል የሚለውን በወጥነት መጠቀም ተመርጧል፡፡

[2]በአንቀጽ 4 እንደተደነገገው የክልሉ መዝሙር መጠሪያም "የትግራይ ብሄራዊ ክልል መዝሙር" የሚል ነው፡፡ በዚኽ ጥናት መዝሙር በማለት ብቻ ጠርቸዋለኹ፡፡

ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፣ የክልሉን መዝሙር ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ምክንያቶችን መመርመር፣ ስለክልሉ መዝሙር የተደነገገውን መተርጎም፣ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው በክልሉ መዝሙር ምን ያኽል እንደተንፀባረቀ መመርመር፣ መተንተን፣ መዝሙሩ የክልሉን ብሔር- ብሔረሰቦች ማንነት ለመገንባትና ለማጠናከር እንዲኹም ሀገራዊ አንድነትን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ፣ የክልሉ መዝሙር ከፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋራ እንዴት ተጣጥሞ አገልግሎት እንደሚሰጥ መፈተሽና በመዝሙሩ የተንጸባረቁትን ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚኽን ዓላማዎች ለማሳካት ጥናቱ፣ የትግራይ ክልልን መዝሙር ለመድረስ ያነሣሡ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? መዝሙሩ የክልሉንና የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ እውነታ ምን ያኽል ያንጸባርቃል? በሕገ መንግሥቱ ስለ ክልሉ መዝሙር የተደነገገው ትርጉም ምንድን ነው? የክልሉን ሕገ መንግሥት ድንጋጌ መዝሙሩ ምን ያኽል በክልሉ መዝሙር አማካይነት በወጣቶች አዕምሮ እንዲሠርጹ የተደረጉት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦች ክልላዊና ሀገራዊ ጠቀሜታ ምን ያኽል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

ጥናቱን ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በክልሉ የመዝሙር ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለመሙላት ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡ ጥናቱም በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የትግራይን ክልል መዝሙር ታሪክ ለመገንዘብ፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገው በመዝሙሩ መንፀባረቁን ወይም አለመንፀባረቁን፣ የክልሉ ክልላዊ ማንነትን ለመገንባትና ለማጠናከር ያለውን ሚና፣ ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከርና ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ፣ እንዲኹም በክልሉ መዝሙር ከፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋራ እንዴት ተጣጥሞ አገልግሎት እንደሚሰጥ ለመረዳት ያስችላል፡፡

በክልሉ ሕገ መንግሥት ስለክልሉ መዝሙር የተደነገገውን መመርመርና መረዳት የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ፩ኛ) የክልሉ መዝሙር እንዲያንፀባርቅ የተደነገገውን ትርጉም ለመረዳት፣ 2) በመዝሙሩ እንዲንፀባረቅ በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገውን ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ ለማወቅ ፣ 3ኛ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው በመዝሙሩ መንፀባረቁን ወይም አለመንፀባረቁን፣ 4) የክልሉ መዝሙር የተደረሰበትን ዓላማ ለማወቅ ያስችላል፡፡

የዚኽ ጥናት የመረጃ ምንጮች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ የትግራይ ክልል ሕገ መንንግሥት፣ የክልሉ መዝሙር፣ የተለያዩ ዐዋጆች፣ በራሪ ጽሑፎችና ታሪክ ነክ መጻሕፍት ወዘተረፈ ናቸው፡፡

የትግራይን ክልል መዝሙር በመረጃነት ለመጠቀም የተቻለው ቋንቋውን በሚችል ሰው ወደ አማርኛ በማስተርጐም ነው፡፡ በትርጉም ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ክፍተት በማሰብ በሌላ የቋንቋው ተናጋሪ ትርጉሙ እንዲመረመር ተደርጓል፡፡ በመለይ (2005) ከተተረጎመው ጋርም እንዲነጻጸር ተደርጓል፡፡ በመገኛ ቋንቋው የተገለጸውን መልእክት ለመረዳት የሚችሉትን አንባቢዎች በማሰብና የመረጃውን ትክክለኛነት ለመግለጽ በመገኛ ቋንቋው የተጻፈውን

በማስቀደምና ትርጉሙን ከሥር በማስቀመጥ ተተንትኗል፡፡ ትንተናው በአብዛኛው ትርጉሙን መሠረት በማድረጉ በጥልቀት ቅርጹን መመርመር አልተቻለም፡፡ በመዝሙሩ የተንጸባረቀው ይዘት የተመረመረውና የተተነተነው የመዝሙሩን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግና ገላጪ የትንተና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ትንተናችን በክልሉ ሕገ መንግሥት ስለ መዝሙሩ የተደነገገውን በመተርጎምና በማስረዳት እንጀምራለን፡፡

## 2) የትግራይ ክልል መዝሙር ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ትርጉም

ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይን ክልል ሕገ መንግሥት ለማጽደቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 4 "የትግራይ ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲኹም የክልሉን ሕዝብ ባህል፣ የትግል ታሪክ፣ አንድነትና ብሩህ ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል (አጽንኦት የተጨመረ ነው፡፡ አጽንኦት የተደረገባቸውን ቃላት ዐውዳዊ አገልግሎት የተሰጠውን ማብራሪያ አባሪ አንድ ላይ ይመለከቷል፡፡)፡፡ ከዚኽ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ መዝሙር ስድስት ጉዳዮችን ማንፀባረቅ አለበት፡፡በቅድሚያ የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም እንመረምራለን፡፡

### 2.1) የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች

ዓላማዎች የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ወደ ፊት የሚፈጸሙ የተለያዩ ተግባሮችን ይጠራል፡፡ የትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ፍትሕን ማስፈን፣ የክልሉን ሕዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች[3] ማስከበር፣ የክልሉን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ማፋጠን፣ የብሔር-ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማክበር፣ በክልሉ ዘላቂ ሰላም ማስፈን፣ እኩልነትንና አንድነትን ማረጋገጥ የሚሉት መኾናቸው በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ተገልጸዋል፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ የተገለጹትንና በተለያዩ አንቀጾች የተደነገጉትን የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በመመርመር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎችን ትርጉም በአጭሩ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ፍትሕን ማስፈን ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡ ፍትሕ የሚለው ቃል የሚገልጸው በሕግ መሠረት ማስተዳደር፣ መዳኘት፣ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ማለት ነው፡፡ ፍትሕን የማስፈን ሥራ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደ ተጠበቀ፣ የትግራይ ክልልን ሕገ መንግሥት የበላይነት በማክበር የሚከናወን ነው፡፡ ይኽም በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (1) "ይህ ሕገ-መንግስት የትግራይ ብሄራዊ ክልል መንግሥት የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም

[3]በትግረይ ክልል ሕገ መንግሥት የተደነገጉት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከተደነገጉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም” በማለት ተደንግጓል፡፡ ይኽም በክልሉ ፍትሕን የማስፈን ሥራ የክልሉን ሕገ መንግሥት የበላይነት በማስከበር ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው፡፡ በመንግሥት አካል የሚሰጥ ውሳኔና የክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦች ልማዳዊ አሠራር የሕገ መንግሥቱን የበላይነት የሚቃረን ከኾነ ተፈጻሚ አይኾንም፡፡ እንደዚኹም፣ የሕገ መንሥቱን የበላይነት የሚቃረን ዐዋጅ፣ መመሪያና ደንብ ተፈጻሚ አይኾንም፡፡ የአስተዳደር ሥራም፣ ፍርድ የመስጠት ተግባርም መከናወን ያለበት የሕገ መንግሥቱን የበላይነት በመጠበቅ ነው ማለት ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳለው በአንቀጽ 37 (1) “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡” በማለት ተደንግጓል፡፡ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍርድ ማግኘት ወይም አስተዳደራዊ ጉዳየዮችን ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል በማቅረብ ፍትሕ ማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው፡፡ ሕግ ተጥሷል ወይም ዲሞክራሲያዊ መብት አልተጠበቀም የሚል ሰው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ፍትሕ ማግኘት ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡

የክልሉን ሕዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበር የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ናቸው፡፡ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ መኾናቸው በአንቀጽ 10 (1) ተደንግጓል፡፡ እነዚኽ መብቶች በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 14 እስከ አንቀጽ 28 ተደንግገዋል፡፡ መብቶቹም በሕይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የነፃነት መብት፣ በኢሰብአዊ መንገድ ያለመያዝ መብት፣ የተያዘ ሰው መብት፣ የተከሰሰ ሰው መብት፣ በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው መብት፣ በወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ ያለመከሰስ መብት፣ በአንድ ወንጀል ድጋሜ ያለመቀጣት መብት፣ የክብርና የመልካም ስም መብት፣ የእኩልነት መብት፣ የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣ የሃይማኖት፣ የኅሊናና የእምነት ነፃነት ሙብት የሚሉ ናቸው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች መካከል አንዱ ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበት የፖለቲካ ሥርዓት መመሥረት ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ በክልሉ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 29 እስከ አንቀጽ 44 ተደንግገዋል፡፡ በተጠቀሱት አንቀጾች የተደነገጉት ዲሞክራሲያዊ መብቶችም አመለካከትንና ሐሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለጽ መብት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ የመደራጀት መብት፣ የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት መብት፣ በመንግሥታዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት፣ የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች፣ የሴቶች መብት፣ የሕፃናት መብት፣ ፍትሕ የማግኘት መብት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ የንብረት መብት፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች፣ የሠራተኛ መብት፣ የልማት መብት፣ የአካባቢ ደህንነት መብት የሚሉት ናቸው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ የእኩልነት መብት ማረጋገጥ ነው፡፡ ይኸም በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25 "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸው ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ የእኩልነት መብቱ በአንቀጽ 8 (1) እና በአንቀጽ 39 የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤት ናቸው ለተባሉት ለትግራይ ብሔር፣ ለኩናማና ለኢሮብ ብሔረሰቦች ተለይቶ የተሰጠ አይደለም፡፡ ድንጋጌው ለኹሉም የሰው ዘር የተሰጠን መብት ይገልጻል፡፡ የክልሉ የሥልጣን ባለቤት መኾናቸው የተገለጹት ብሔር-ብሔረሰቦች የእኩልነት መብት የሚኖራቸው ሰው በመኾናቸው ብቻ ነው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች መካከል የዲሞክራሲያዊ መብቶች አካል የኾነው የብሔር-ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማክበር የሚለው ይጠቀሳል፡፡ ይኸ መብት በትግራይ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የትግራይ ብሄር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ መኾኑ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ተደንግጓል፡፡[4] በዚኹ መሠረት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች የየራሳቸውን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲኹም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማክበርና የማስፋፋት መብት ያላቸው መኾኑ ተደንግጓል፡፡ በክልሉ የሚኖሩ በስም የተጠሩት ብሔር-ብሔረሰቦች በየራሳቸው መልክዓ-ምድራዊ ክልል ውስጥ የየራሳቸውን ጉዳይ በየራሳቸው የመጨረስና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እንዲኹም በፌዴራሉ መንግሥት ውስጥ በነፃነት፣ ተገቢና ፍትሐዊ በኾነ ውክልና ተሳትፎ የማድረግ መብታቸው ተረጋግጧል፡፡ መብቶቻቸውም በየሰፈሩበት መልክዓ-ምድር እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩባቸውን መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራሉ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘትን ያጠቃልላል፡፡

የክልሉ መንግሥት "በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት" እንዳለበት በአንቀጽ 98 (1) ተደንግጓል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ "ሕዝብ" የሚለው የወል መጠሪያ በክልሉ የሚገኙትን የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች መኾኑን በአንቀጽ 39 ተደንግጓል፡፡ ይኸም ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያላቸው በአንቀጽ 8 (1) የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤት መኾናቸው የተደነገገውና

[4]ይኸ መብት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (1) "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ ይኸ መብት በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት የተጠበቀ መኾኑ የተደነገገው የፌዴራሉን ሕገ መንግሥት ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በአንቀጽ 39 በስም የተጠቀሱት ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በክልሉ ለሚኖሩ ሌሎች "ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" አልተሰጠም ማለት ነው፡፡

ብልጽግናን ማምጣት ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በክልሉ ሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው፣ የትግራይ ክልል ሕዝቦች ለዘመናት ተንሰራፍቶ በቆየው አፋኝ ሥርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ታፍነው፣ በተዛቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ኋላ ቀርነት ተጋልጠው መቆየታቸውን በአጠቃላይ በዕድገታቸው ላይ ያደረሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ መኾኑ ተገልጿል፡፡ ስለኾነም፣ ክልሉን ለማበልጸግ ለድህነትና ኋላ ቀርነት የዳረጉትን የተዛቡ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን በማስወገድ የትግራይ ክልል ሕዝብ ለኢኮኖሚ ዕድገት እንዲበቃ በሚያስችሉ ፖሊሲዎች መተካት የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ ይኸም በክልሉ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ ያስችላል፡ የተዛቡ ማኅበራዊ ፖሊሲዎችን በማስወገድ በአንቀጽ 100 እንደ ተደነገገው "የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ ቤትና ማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡" ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች መካከል የተወሰኑት በክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ኀላፊነት ብቻ የሚተገበሩና ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር በመተባበር የሚተገበሩ ናቸው፡፡ በክልሉ ሥልጣንና ኀላፊነት የሚተገበሩ ዓላማዎች፣ የትግራይን ክልል "ህዝቦች" ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያፈኑትን፣ ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ዲሞክራሲ እንዲበቃ ማስቻል የሚሉት ናቸው፡፡ በተጨማሪም በክልሉ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ዐሥር ከአንቀጽ 98 እስከ 102 የተደነገጉትን የክልሉ ፖሊሲ፣ መርሆዎችና ዓላማዎችን (ፖለቲካ ነክ፣ ኢኮኖሚ ነክ፣ ማኅበራዊ ነክ፣ ባህል ነክና የአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ዓላማዎች) መተግበር የትግራይ ክልል መንግሥት ኀላፊነት ነው፡፡ ኾኖም፣ ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር በበጀት የተሳሰረ፣ በሀገር አቀፍ የልማት ሥራዎች የተቀናጀ በመኾኑ የፌዴራል መንግሥት የኀላፊነት ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋራ በመተባበር የሚተገበሩት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ደግሞ የኹሉንም ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበር፣ ኢትዮጵያ በሕገ መንግሥት ብቻ እንድትመራ ማድረግ፣ "የግለሰብ መብቶችና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት የተከበረበት በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የነገሠበት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትን ማጠናከር፤ ማጎልበት፤ የጋራ ዕድገትን ማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰብ መገንባት" የሚሉት ናቸው፡፡

## 2.2) የክልሉ ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሌሎች ብሔር-ብሔረሰቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነት

የትግራይ ክልል መዝሙር የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት የሚያንጸባርቅ እንዲኾን በአንቀጽ 4 መደንገጉ ቀደም

ሲል ተገልጿል፡፡ በመኾኑም “የክልሉ ሕዝብ” የሚለው የትግራይ፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው፡፡ “የኢትዮጵያ ሕዝቦች” የተባሉት ደግሞ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 8 (1) እንደተደነገገው የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች የኾኑትን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የትግራይ ክልል መንግሥትን ከኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነት እንዲኖረው ያደረገውን ምክንያት በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ፡-

> የሀገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በ[ባ]ካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ሥርዓት በሚያስተማምን ኹኔታ ተደምስሶ ኢትዮጵያ ሀገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የተከበሩበት፣ በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የነገሠበት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማሕረሰብ ለመገንባት ያለው[ን] ጠቀሜታ በመገንዘብ

በማለት ይገልጻል፡፡

የትግራይ ክልል መዝሙር እንዲያንፀባርቅ የተባለው የትግራይ ክልል ሕዝብ ከኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነት የሚረጋገጠው ኹሉም ክልሎች ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሠርቱ ነው፡፡ ይኸም የሚረጋገጠው እያንዳንዱ ክልል በሚተዳደርበት ሕገ መንግሥት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋስትና ሲሰጥና ክልሉን በሚመራው መንግሥት ተግባራዊነቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡[5] የየክልሉ ሕገ መንግሥት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋስትና መስጠት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይ ሕግ መኾኑን በመጠበቅ ነው፡፡ ይኸም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (1) የተደነገገውን መጠበቅ አለበት፡፡ ስለኾነም የክልሎች ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መከተል የሚመነጨው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 28 እስከ አንቀጽ 44 የተደነገጉትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማክበር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመኖርን እምነት እውንነት ያረጋግጣል፡፡

[5]የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች እንዲከበሩ መጣርና ማክበር አብሮ የሚኖረውን ሕዝብ ማንነት ከማክበር ይጀምራል፡፡ ስለኾነም፣ ክልሉን በበላይነት የሚመሩት የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋራ አብሮ በሰላም ለመኖር ከማመን በፊት በክልሉ የሚኖሩትን ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ማክበር ግድ ይላል፡፡ የሌሎችን ማንነት ሳያከብሩ ዴሞክራሲንና ሰላምን በዘላቂነት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በክልሉ ያሉ የኹሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች መብት ሳያከብሩ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ዘላቂ ሰላምና ጠንካራ ዴሞክራሲ መገንባትም አይቻልም፡፡ እንደዚኹም የኹሉም ሕዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረዋል፤ ሀገሪቱም የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች በትክክል ተተርጉመዋል ማለት አይቻልም፡፡

"ሁሉም ህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበሩ፣ በህገ መንግሥትና በሱ ብቻ የምትመራ ሃገር እንድትሆን በማመን፣" "በአብዛኛው የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ላይ ይፈፀም በነበረው አንገፍጋፊ ጭቆና ተጎጂ ኾነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፣" ይኽም አብዛኛው ሕዝብ ተበዳዬ ከነበረ ጥቂቶቹ ደግሞ በዳዬ ነበሩ ወይም አልተበደሉም ማለት ነው፡፡ ይኽ ዓይነቱ የተዛባ ግንዛቤ "አልተበደለም" በሚባለውና "ተበድለዋል" በሚባሉት መካከል በታሪክ አለመግባባትን ያስከትላል፤ የአንድነት ስሜትን ያላላል፤ የወደፊት የጋራ ዕድገትን ለማምጣት በሚደረግ እንቅስቃሴ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡

## 2.3) የትግራይ ክልል ሕዝብ ባህል

የክልሉ መዝሙር የትግራይን ክልል ሕዝብ ባህል የሚያንጸበርቅ እንዲኾን በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡ ይኽ ድንጋጌ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 (1) የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች እያንዳንዳቸው የራሳቸውን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲኹም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አላቸው የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የባህል ክፍል የኾነው ቋንቋ በትግራይ ክልል ዘንድ እኩል ዕውቅና እንደሚኖራቸው በአንቀጽ 5 (1) ተደንግጓል፡፡ በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 5 (1) በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግሥት እኩል ዕውቅና እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡ ይኽ ድንጋጌ የሚመለከተው በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ዕውቅና የተሰጣቸውን የትግራይ፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔር-ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ነው፡፡ በዚኽ አንቀጽ ዕውቅና ያልተሰጣቸውን ብሔር-ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የዐማርኛን ቋንቋ ጨምሮ አያካትትም፡፡ ቋንቋቸው ዕውቅና የተሰጣቸው የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች ይኹን እንጂ፣ በአንቀጽ 5 (2) እንደተደነገገው የትግራይን ክልል የሥራ ቋንቋ ትግርኛ ነው፡፡ ይኽም የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች ከየራሳቸው ቋንቋ በተጨማሪ የብሔራዊ ክልሉን የሥራ ቋንቋ ትግርኛን መማርና መናገር ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

በአንቀጽ 101 (1) "መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብአዊ ክብርን እንዲኹም ለዲሞክራሲው ሕገ መንግሥትን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኀላፊነት አለበት" በማለት በክልሉ ሕገ መንግሥት ተደንግጓል፡፡ እንደዚኹም በክልሉ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ 101 (2) መንግሥት አቅሙ በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን የማስፋፋት ግዴታ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ዕውቅና አልተሰጠም፡፡ የብሔረሰቦች ባህል፣ ልማድና ኪነጥበብ ክልላዊ መንግሥቱ እንዲጎለብት፣ እንዲፋፋ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ለትግራይ ብሔር፣ ለኢሮብና ለኩናማ ብሔረሰቦች ነው፡፡ እነዚኽ ብሔር-ብሔረሰቦች በቋንቋቸው እንዲማሩ፣ ባህላቸውን ለመግለጽና ለመንከባከብ እንዲችሉ፣ በታሪካቸው እንዲኮሩ ሲደረግ በክልሉ የሚኖሩት የዐማራ ብሔር ተወላጆች በቋንቋቸው የመማር ዕድል አልተሰጣቸውም፡፡ ለዕለት ተዕለት ተግባሮቻቸው የዐማርኛ ቋንቋን የመጠቀም መብታቸው የተገደበ ነው።

**2.4) የትግራይ ሕዝብ የትግል ታሪክ**

የትግራይ ሕዝብ የትግል ታሪክ በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ ተደንግጓል፡፡ ይኸው የሕዝቡ የትግል ታሪክም በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ "የትግራይ ሕዝብ ያለፉት ጨቋኝ ሥርዓቶችን ለመደምሰስ ወደር የሌለው መሥዋዕትነት" ከፍሏል በማለት ተገልጿል፡፡ ያለፉት ጨቋኝ ሥርዓቶች የተባሉትም በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፣ በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴና በወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተመሩት ሥርዓተ መንግሥቶች ናቸው፡፡ የዚኸ ሐሳብ ማስረጃ በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት በ1968 ዓ. ም. ባወጣው መግለጫ ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ኃይሏ በርትቶ ባካባቢዋ የነበሩትን ነገሥታት በቁጥጥሯ ሥር አውላ ነበር፤ ይሁን እንጂ አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክ አማካኝነት ትግራይ በሸዋው ማእከላዊ ግዛት ሥር ወደቀች፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የመሳፍንት ቡድንና ተከታዮቹ የትግራይን ነፃነት ገፈው የሕዝቧን አንድነት አናጉት፡፡ ግልጽና ስውር በሆኑ ዘዴዎችም (ሸዋዊ ዘይቤዎች) የትግራይ ሕዝብ በድንቁርና፣ በበሽታ፣ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰምጥ ያደረጉት፡፡ በተለይም ትግሬነቱን በፍጥነት እንዲክድና ያለውድ በግድ "አማራ ለማድረግ" ያልሞከሩት ዘዴ ባይኖርም መሬቱ ተቆራርሶ ስለተወሰደበትና የተደራረበ ጭቆና ስለደረሰበት አገሩን ጥሎ ተሰደደ፡፡ ባጠቃላይ ባሁኑ ጊዜ ትግራይ ነፃነቷ የተገፈፈች፣ መሬቷ ተቆራርሶ የተወሰደባትና የተወሳሰበ ችግር የደቀሰው ሕዝብ የሚኖርባት ጭቁን ብሔር ናት (በትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት፣ 1968፤ V-VI)፡፡

ይኸንን በትግራይ ሕዝብ ላይ ደረሰ የተባለውን በደል ከ80 ዓመታት በላይ ትግል ሲደረግ ቆይቶ "የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት" መመሥረቱ በድርጅቱ መግለጫ ተገልጿል፡፡ ይኸም ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ በ1881 ዓ. ም. መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ ሥልጣነ መንግሥቱን ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በመውረሳቸው የተከፉ የጠቅላይ ግዛቱ መሳፍንት በተለያዩ ጊዜያት በማዕከላዊው መንግሥት ላይ ተቃውሟቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚኸ ድርጊት የትግራዩ መስፍን ራስ መንገሻ ዮሐንስ የፈጸሙት አመፅ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡ የዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ሥልጣነ መንግሥት ሕጋዊ ወራሺ "እኔ ነኝ" ይሉ የነበሩት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክን ለማጥቃት ኤርትራን በቅኝ ይገዛ ከነበረው ከኢጣልያ የጦር መሪ ጋር ኹለት ጊዜ በመሀላ ስምምነት አድርገዋል (ገብረ ሥላሴ፣ 1958)፡፡ ከተቃዋሚ መሳፍንት መካከል የዐፄ ኃይለ ስላሴ አማች የልዕልት ዘነበወርቅ ባል፣ የዐፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የነበሩት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ይጠቀሳሉ፡፡ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ በ1928 ዓ. ም. ከትግራይ ተነሥተው ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ኤርትራ በመኼድ ኢትዮጵያን እያጠቃ የነበረውን የኢጣልያን ጦር ተቀላቀሉ፡፡ እሳቸውም ወታደሮቻቸውን ከኢጣልያ ጦር ጎን አሰልፈው የኢትዮጵያን ጦር ወግተዋል፡፡ ኢትዮጵያን ካጠቃው የኢጣልያ ጦር ጋር ተሰልፈው የኢጣሊያንን ሰንደቅ ዓላማ አዲስ አበባ ላይ ሰቀሉ፡፡ ኢትዮጵያን ከወረረው ከኢጣሊያ ጦር ጎን የመሰለፋቸው ምክንያት የዐፄ ዮሐንስ ሥልጣን መንግሥት በሸዋው ተወላጅ ዐፄ ምኒልክ ተነጥቀናል የሚል ነበር ፡፡

የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያውያን ዐርበኞችና በእንግሊዝ ጦር ድጋፍ ድል ኾኖ ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ “በ1934 ዓ. ም. በዋጀራት አካባቢ የተጣለውን የገንዘብ ቅጣት አንከፍልም በማለት የተጀመረው ፀረ-መንግሥት አመፅ ወደ ሌሎች የትግራይ አካባቢዎች ተዛመተ፡፡” የደገፈው የእንደርታ፣ የራያ፣ የምሥራቅ ትግራይና የከፊል ተምቤን ሕዝብ አመፁን ደግፎ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ የተሾሙትን ከሥልጣን አስወገደ፡፡ አመፁ የትግራይን ዋና ከተማ ከተቆጣጠረ በኋላ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ “በእንግሊዞች የሠለጠነውን አዲሱን ጦራቸውን አሰልፈው የእንግሊዝ መኮኖችን በመሪነትና በተዋጊነት አሳትፈው ወያኔዎችን ተዋጉ፤ ዐመፁንም ተቆጣጠሩ፡፡” (ገብሩ፣ 2007፤ 23) የአመፁ ምክንያት በተመሳሳይ መንገድ እንደሚከተለው ይገለጻል፡፡ “የትግራይ ሕዝብ በቅጣት ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፍል ተደርጓል፤ የገበሬው መሬት እየተነጠቀ ለመንግሥት ታማኞች ተከፋፍሏል፤ በኢጣልያ ጊዜ ይከፍለው ከነበረው ዐምስት እጥፍ የበለጠ ግብር እንዲከፍል ተደርጓል፣ ማዕከላዊ መንግሥትን በማጠናከር ስም የጠቅላይ ግዛቱን የሥልጣን ወራሾች ሥልጣን በመንጠቅ ለሸዋ ገዥ መደብ ተሰጥቷል” የሚሉ ወገኖች ሕዝቡን በመቀስቀስና በማስተባበር “ወያኔ” በሚል ስም ተሰባስበው ገበሬዎችን አደራጅተው በማዕከላዊና በደቡባዊ ትግራይ ዐመፁ፡፡ በ1943 (እ. አ. አ.) መቀሌን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች የእንግሊዝ መንግሥት ሮያል አየር ኃይል ከአየር ወደ መሬት በወረወራቸው ቦንቦች አመፁ ተገታ (Aregawi, 2004: 572)፡፡ የአማፅያኑን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ምክንያት የሚደግፉ ወገኖች ቂማቸውን ቋጥረው ጊዜ መጠበቅ ትግሉን መቀጠላቸው ይናገራል፡፡ በዐመፁ በብዛት የተሳተፉት የራያ አካባቢ ነዋሪዎች ነበሩ (ሲሳይ፣ 2010)፡፡

የክልሉ መሳፍንትና መኳንንት የመንግሥት ሥልጣንን ወደ ትግራይ ለመመለስ ያደረጉትን ትግል ፈለግ የተከተሉ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይማሩ የነበሩ የጠቅላይ ግዛቱ ተወላጅ ተማሪዎች ትግሉን ቀጠሉ፡፡ በ1962 ዓ. ም. የተጸነሰው የትግራይ ተራማጆች እንቅስቃሴ የብሔረ ትግራይ ተራማጆች ድርጅት (ተ.ኀ.ሓ. ት) በሚል ስም ለስድስት ወራት ያኽል ምሥጢራዊ ድርጅትና ወታደራዊ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ. ም. የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት (ተ.ኀ.ሓ. ት.) መሠረቱ፡፡ ድርጅቱም ጭቁኑ የትግራይ ሕዝብ ከሰማንያ ዓመት በላይ ታግሎ የመሠረተው የፖለቲካ ድርጅት ነው (የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፣ 1968) ወደ ጫካ በመግባትም ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግን መታገል ጀመሩ፡፡ የትግራይሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት[6] በ1968 ዓ. ም. ባወጣው “መግለጫ” “የትግራይ ሕዝብ ለረጅም ዘመን ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቱ ተነፍጎ ሲጠላና ሲናቅ እንዲኾም አድልዎ ሲፈጸምበት ቆይቷል፡፡ በተለይም ከምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ፀረ-ሸዋዊ የመሳፍንቶች ሥርዓትና ፀረ-ብሔራዊ ተፅዕኖ የኾነ የተደጋገመ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አካኼዷል፡፡ ለምሳሌም በወያኔ ጊዜ ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ተፅዕኖ የተደረገው ዲሞክራሲያዊ የትጥቅ ትግል ምን ጊዜም የማይረሳ ነው፡፡” (የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፣ 1968፤ 17) ከዐፄ ምኒልክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዘለቀው “የሸዋ መሳፍንት ሥርዓት” የሚፈጸምበትን የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የፖለቲካ መገለልና

[6] ድርጅቱ በተለያየ ስም የተጠራ ሲኾን በአኹኑ ጊዜ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር በመባል ይጠራል፡፡

አድሎ የደረሰበትን፣ የጥላቻና የንቀት ስሜት በማስቀረት ክብሩን ለማስጠበቅ የትግራይ ሕዝብ ተደጋጋሚ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አካኺዷል፡፡ በቀዳማዊ ወያኔ ያደረገው እንቅስቃሴ የኃላ ነበር፡፡

ፀረ-የሸዋ መሳፍንት ሥርዓት እና ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ተፅዕኖን ለመታገል የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ. ም. የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሥልጣኑን በወታደራዊ መኮንኖች ተነጠቀ፡፡ ይኸ መኾኑ እየታወቀ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅትን ማቋቋም ያስፈለገበትን ምክንያት ኃይለሥላሴን የተካውን የወታደራዊ መኮንኖች ስብስብ "ፋሽስታዊ ወታደራዊ መንግሥት" ብሎ በመፈረጅና የሚያደርገውን እንቅስቃሴም "ንኡስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ" ነው ብሎ በማመን ነበር፡፡ "በፋሽስታዊ ወታደራዊ መንግሥት በመካሄድ ላይ ያለው ጠጋኝ ለውጥ ምክንያት ሊደርስ የቻለው የባሰ ጭቆና ሊጠፋ የሚችለው በተደጋገመ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡" ብሎ አመነ፡፡ እምነቱን ወደ ተግባር ለመተርጎም "የብሔረ ትግራይ ሕዝብ ነፃነት የሚገኘው በትጥቅ ትግል ብቻ መሆኑን በመገንዘብና ታሪካዊ ግዳጁን ለመፈጸም ተ.ሓ. ህ. ት. ተብሎ የሚጠራ ብሔራዊ አብዮታዊ ግንባር አቋቋመ፡፡" (የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፣ 1968፤ VIII-IX)) በሽምቅ ውጊያም የኢትዮጵያን ወታደራዊ መንግሥት መፋለም ቀጠለ፡፡

የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት የሽምቅ ውጊያ ሲያካኼድ ኢትዮጵያዊ የኾኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን አጥቅቷል፡፡ የኤርትራን የነጻነት ትግል ያራምድ ከነበረው ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሕግሓኤ) ጋር ደግሞ ከፍተኛ ትብብር አድርጓል፡፡ ይኸንን በአጭሩ እንመልከት፡፡

የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ግጭት ውስጥ በመግባት ጥቃት ከፈጸመባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ (ግገሓት) ይጠቀሳል፡፡ ይኸ የፖለቲካ ድርጅት "ለትግራይ ነጻነትና ከዚያ ባሻገርም ለትግራይና ኤርትራ ኅብረት የቆመ ድርጅት ነበር፡፡ ከኤርትራ ድርጅቶች መካከልም ከጀብሃ ጋራ ብርቱ ቁርኝት ነበረው፡፡ ግገሓት የያዘው አቋም በበርካታ ወጣት የትግራይ ምሁራን በተለይም በተሓህት አባላትና ደጋፊዎች ተቀባይነት አላገኘም ነበር" (ገብሩ፣ 2007፤ 49)፡፡ ድርጅቱ ከተሓህት ጋራ እንዲዋሕድ በተደረገበት ከፍተኛ ግፊት ለድርድር ፈቃደኛ ኾነ፡፡ ሠራዊታቸውን ለማዋሐድ ድርድር የሚደረግበት ቀን ተቀርጦና ቦታ ተወስኖ ከተሓህት አመራር ጋራ ተገናኙ፡፡ ውሕደቱ እንዲካኼድ ስምምነት ላይ ተደርሶ የግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ ሠራዊትና የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ሠራዊት አባላት "አንድ ለአንድ" አብረው እንዲተኙ ተደረገ፡፡ የተሓህት ሠራዊት ኀሕ ሲቀድ አብሮት የተኛውን የግገሓት ሠራዊት አባል ትጥቅ እንዲያስፈታና እጅ እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ ትጥቅ አልፈታም ባለው ላይም ርምጃ በመውሰድ ሕይወቱን ቀጠፈ፡፡ ትጥቅ የፈታውን ተራ ታጋይ በምርጫው ትግሉን እንዲቀላቀል ወይም ወደመኖሪያ ቀዬው እንዲኼድ ፈቀደ፡፡ በድርድሩ ተሳታፊ የነበረውን አመራር ግን አስሮ ዘብጥያ ላካቸው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ከፍተኛ አመራር የነበሩት ገብሩ (2007) በግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ ላይ የተወሰደው ርምጃ ቅንነት የጎደለው፣ ትክክለኛ ያልነበረ፣ ከተጠያቂነትም የማያድን ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ ይኸ ዓይነት ስሕተት የተፈጸመበት የትግል

ታሪክ የሚታፈርበት እንጂ የሚኮራበት አይደለም፡፡ ታሪኩ በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ ማድረግም ትውልዱ ወደፊት ይዞት እንዲዘልቅ ማድረጉ ትክክል አይደለም፡፡

በክፍለ ሀገሩ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲና የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት ሠራዊት አባላትን ወግቷል፤ አጥቅቷል (ገብሩ፣ 2007)፡፡ ጥቃቱን የፈጸመበት ምክንያት ሲመረመር አጥጋቢ አለመኾኑ የፖለቲካ ድርጅቱን ወንጀለኛ ያደርገዋል፡፡ ይኸም ድርጊት የሚኮራበት የትግል ታሪክ አይደለም፡፡ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የተደራጁትን በጦርነት ማሸነፍን ማስተማር ትውልዱ ልዩነትን በመወያየትና በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ በኀይልና በግድያ በማሸነፍ መፍታትን እንዲማር ያደርጋል፡፡ ይኸም የማይመረጥና ኋላ ቀር አስተሳሰብ እንዲቀጥል ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

ህወሓት ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን የወጋው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ይዋጋ ከነበረው የኤርትራ ነጻነት ግንባር ጋራ በመተባበር ነው፡፡ ተሓህት ኤርትራ በመግባት ከኤርትራ ነጻነት ግንባር ጎን ተሰልፎ የኢትዮጵያን ሠራዊት ወግቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመነጠል ይዋጋ የነበረውን ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራን በመደገፍ ለስኬቱ መሥዋዕትነት መክፈል የኤርትራን ጥያቄ "የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው" ብሎ መቀበል በሰከነ አእምሮ እውነተኛውን ታሪክ ለሚረዳ ትውልድ የሚኮራበት ታሪክ ሳይኾን የሚያሳፍርና በታሪክም የሚያስወቅስ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች በተደረጉ ውጊያዎች የኤርትራ ነጻነት ግንባር መካናይዝድ ኀይልን ማሰለፍ፣ አዲስ አበባንም መቆጣጠር የትግል ታሪክ የተባለው ከኢትዮጵያ ጥቅም ተጻራሪ ኀይል ጋራ የነበረውን ትብብር ይዘክራል፡፡ የኢትዮጵያን የባሕር በር ሙብት እንደ ቀላል ንብረት አሳልፎ መስጠት የትግል አሉታዊ ውጤት በመኾኑ የታሪክ ተወቃሽነትን ያስከትላል፡፡

ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማነጠል ይዋጋ ከነበረው ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ጋራ መተባበር የኢጣሊያን ቅኝ ገዢ ጦር ለመውጋት ወደ ሰሐጢ ዘምተው ዶጋሊ ላይ በ1879 ዓ. ም. የኢጣልያን ጦር ድል ያደረጉትን ራስ አሉላ አባ ነጋን ታሪክ (ተክለ ጻድቅ፣ 1982) መጻረር ነው፡፡ ራስ አሉላ የተዋጉለትን ዓላማ የሚጻረር ተግባር ፈጽሞ፣ ለራስ አሉላ ሐውልት መሥራትና የመቀሌን አውሮፕላን ማረፊያ በእሳቸው ስም መጥራት የታሪክ ተቃርኖ ነው፡፡

የትግራይ ትግል ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በመተባበር እንደ ነበር በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ "መላ የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ስርአት በሚያስተማምን ሁኔታ" መደምሰሱ ተገልጿል፡፡ የትግራይ ትግል ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋራ እንደተደረገ የተባለበት ምክንያት፣ አንድም በ1972 ዓ. ም. ከተመሠረተው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን)፣ በኋላም ከኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) ጋራ በመተባበር እስከ 1983 ዓ. ም. በዘለቀ ጦርነት ወደ ሥልጣን መጣ፡፡ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የተለያየ ባህል፣ የተለያየ ቋንቋ፣ የተለያየ ሥነ ልቦና ወዘተ. ከነበራቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላት ጋራ ግንባር ፈጥሮ በመታገሉ ነው፡፡ አንድም፣ የተለያዩ ብሔሮችን ነጻ ለማውጣት ይታገሉ ከነበሩ ለምሳሌ፣ የሲዳማ ዐርነት ንቅናቄ (ሲዐን)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ)፣ የኦሮሞ ነጻነት

ግንባር (ኦነግ) ጋራ የትግል አጋርነት በመፍጠር በመታገሉ ነው፡፡ አንድም፣ በወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተከፋ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለውጥ በመፈለጉ ምክንያት የሽምቅ ውጊያ ያካኼዱ የነበሩትን ኀይሎች በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመደገፉ ነው፡፡ ይኸም ኾኖ፣ ኹሉም ኢትዮጵያዊ ለውጡን ለማምጣት እኩል ተሳትፎ ነበረው የሚለው ፖለቲካዊ አገላለጽ ትክክለኛውን ታሪካዊ እውነታ አያስረዳም፡፡ በመዝሙሩ እንዲንጸባረቅ የተደረገው የትግል ታሪክ የተፈጸመ ነው? ለሕዝቡ ምን ጥቅም አስገኝቷል? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አሉታዊነቱ ያመዝናል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ የሚጋራው አኩሪ ታሪክ እንዳለው ቢታወቅም፣ በመዝሙሩ እንዲንጸባረቅ አልተደነገገም፡፡ ይኸም በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ የተባለው ታሪክ ትውልዱ ያባቶቹን የቀደመ ታሪክ ለማወቅ የማያነሣሣ፣ የሀገር ሉዓላዊነትን ለመጠበቅ የተከፈለውን መሥዋዕትነት የማይነግር፣ በዶጋሊና በዐድዋ የተገኘውን ድል የማያስታውስ፣ ማይጨው ላይ የተከፈለውን መሥዋዕትነትና የዐምስቱን ዓመት የዐርበኝነት ተጋድሎ ለትውልድ የማይነግር፣ የ1969 ዓመተ ምሕረትን የሶማሌ ወረራን ለመመከትና ከሀገር ለማስወጣት የተከፈለውን መሥዋዕትነት የማያስታውስ ነው፡፡ በመዝሙሩ እንዲንጸባረቅ የተባለው ታሪክ ትውልዱ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር ከ1967 እስከ 1983 ያደረገውን ትግል ብቻ እንዲያስብ፣ እንዲገነዘብ፣ እንዲረዳ፣ እንዲያደንቅ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ የትግራይ "ሕዝብ" የትግል ታሪክ በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ መደረጉ ትውልድን የሚያኮራና በአርኣያነት የሚጠቀስ ኾኖ አይቀጥልም፡፡ መዝሙሩ የትግራይን ሕዝብ የትግል ታሪክ እንዲያንጸባርቅ የሚለው ከሥልጣን ለውጥ በኋላ በኢትዮጵያውያን መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት መኾኑን ያላገናዘበ ነው፡፡

በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ የተባለው የትግል ታሪክ ለትግራይ ክልል "ሕዝብ" በተለይ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ ምን አስገኘ? ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይፈጽም የነበረውን የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ እስራትና ግድያ ማስወገድ በራሱ ግብ አይደለም፡፡ ከደርግ ሥልጣን መወገድ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን የተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት ተፈጠረ? የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተዳደር ቋንቋንና የብሔረሰብ አሰፋፈርን መሠረት ባደረገ የፌዴራል አስተዳደር በመዋቅርና በማንነት ላይ የሚያተኩር የፖለቲካ ሥርዓት እንዲራመድ በግንባር ቀደምነት በመምራቱ የትግራይን "ሕዝብ"ም ኾነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለክፍፍልና ለመፈናቀል፣ ለግጭትና ለሞት ዳረገ፡፡ ዛሬ በሀገራችን የተከሠተውን ችግር ኢትዮጵያዊነትን ወደ ጎን በመግፋት በዘርና በቋንቋ መሠረት ላይ ቆሞ መፍታት አስቸጋሪ ነው፡፡ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገው የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የትግል ታሪክ በአሉታዊነት የሚታወስ እንጂ የሚኮራበት አይኾንም፡፡

### 2. 5) የክልሉ ሕዝብ አንድነት

የትግራይ ክልል መዝሙር እንዲያንጸባርቅ ከተደነገጉት መካከል "የክልሉን ሕዝብ አንድነት የሚያንጸበርቅ ይሆናል" የሚለው አንዱ ነው፡፡ በአንቀጽ 98 (2) "መንግስት የብሔረሰቦችንና

የሕዝቦችን[7] ማንነት የማክበር፣ በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡ በተለይ ይበልጥ ኋላ ቀር ለሆኑት ብሄረሰቦች ልዩ ትኩረት በማድረግ እኩልነታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ መንግሥት በክልሉ የትግራይ፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔር-ብሔረሰቦች በቋንቋቸው በመጠቀም፣ ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ማንነታቸው እንዲከበር መደረጉንና በክልሉ ቴሌቪዥን መርሐ ግብር ተሰጥቷቸው በቋንቋቸው ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያቀርባሉ፡፡ በእነዚኽ ብሔር-ብሔረሰቦች መካከል እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን በማጠናከር መንግሥት በተግባር ግዴታውን መወጣቱን ለማረጋገጥ ግን ተጨማሪ ሥራ ይጠይቃል፡፡ በክልሉ ይበልጥ ኋላ ቀር የኾኑ "ብሔረሰቦችን" ለይቶ ለመረዳትና ከሌሎች ብሔር-ብሔረሰቦች ጋር እኩልነታቸውን ለማረጋገጥ በመንግሥት የተሠራውን ሥራ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ክልሉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተደነገጉት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ድንጋጌዎች ከተከበሩና የትግራይ ብሔር፣ የኩናማና የኢሮብ ብሔረሰቦች አንድነት ይጎለብታል፡፡ በክልሉ የሕግ የበላይነት እንዲነግሥ ከተደረገ፣ በክልሉ የሚኖሩት የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች የየራሳቸውን ማንነት መጠበቅና ማስከበር ከቻሉ፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን መንከባከብና ማበልጸግ የሚችሉበት ኹኔታ ከተመቻቸ፣ እንዲኹም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት ካገኙ፣ ራሳቸውን በራሳችው ማስተዳደር ከቻሉ፣ የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው ከተከበረ በክልሉም ኾነ በፌዴራል በሚገኙ የሥልጣን እርከኖች ተገቢው ውክልና ካገኙ የክልሉ "የሕዝብ አንድነት" ይጎለብታል ብሎ ከማሰብ የመነጨ ነው፡፡ ይኹን እንጂ ያፀደቁት ሕገ መንግሥት በቋንቋ ማንነት ላይ የተመሠረተ ከመኾኑም በላይ ያልተተገበረ በመኾኑ በክልሉ የሥልጣን ባለቤቶች በተባሉት መካከል ከአንድነት ይልቅ ጥላቻና መራራቅ መንገሡን ማስተዋል ይቻላል፡፡

በመዝሙሩ የሕዝቡ ብሩህ ተስፋ እንዲንጸባረቅ በማለት በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገው ሐሳብ በሕገ መንግሥቱ መግቢያ "ሁሉም ህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረው፤ በሕገ መንግሥትና በሱ ብቻ የምትመራ ሃገር እንድትኾን በማመን"፤ "የክልሉ ህዝቦች የተከበሩበትና ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ መዋል መቻላቸውን በማመን" በማለት ተገልጸዋል፡፡ ከዚኽም በላይ የኹሉም ሕዝቦች መብቶች በክልሉ ሕገ መንግሥት በተለያዩ አንቀጾችም ተደንግገዋል፡፡

በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባርቁ የተደነገጉት አብዛኛዎቹ በክልሉ የሞኖሩትን ብሔር ብሔረሰቦች የሚያስማሙ ይመስላሉ፡፡ የፖለቲካ ድርጅቱ የትግል ታሪክ ይክልሉ ሕዝብ ታሪክ ተደርጎ መቅረቡ ትክክል አይመስልም፡፡ የራስን እድል በራስ መወሰን መብት እስከ መገንጠል በሚለው ሐሳብ መገንጠል እንደመብት መቁጠር ትክክል አይደለም የሚሉ በርካቶች ናቸው፡፡ ከኹሉም በላይ መዝሙሩ እንዲያንጸባርቃቸው የተደነገጉት ሕገ

[7] ብሔረሰቦች የሚለው መጠሪያ ኢሮብና ኩናማ የተጠሩበት መኾኑን ከአንቀጽ 39 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ይኽ መጠሪያ የትግራይ ብሔር በማለት የተጠራውን አያካትትም፡፡ ሕዝቦች የሚለው መጠሪያ የትግራይ ክልል የበላይ ሥልጣን ባለቤት በተባሉት መጠሪያው አልተካተተም፡፡

መንግሥታዊ መብቶች በክልሉ የሚኖሩትን ኹሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የማይመለከቱ ናቸው፡፡ በክልሉ የሚኖረው ዐማራ በቋንቋው፣ በማኅበራዊ አመጣጡ ልዩነት ይደረግበታል፤ በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ አይደረግለትም፤ ማንነቱ አይከበርለትም፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (1-3) በተደነገገው መሠረት በትግራይ ክልል የሚኖረው ዐማራ በራሱ ቋንቋ የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የማገለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲኹም ታሪኩን የመንከባከብ መብት የለውም፡፡ በቋንቋው ለመማርና ለመዳኘት፣ ባህሉን ለማገለጽና ለመንከባከብ፣ በታሪኩ ለመኩራት፣ በሚኖርበት መልክዓ ምድር ራሱን በራሱ ለማስተዳደር አይችልም፡፡ በክልሉ አስተዳር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የለውም፡፡ "በትግርኛ ቋንቋ አንማርም" የሚሉ የአላማጣ ነዋሪዎች ትምህርታቸውን ለማቋረጥ መወሰናቸው መብታቸው ያለመከበሩ ውጤት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፤ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የመምረጥና የመመረጥ መብት ቢኖረውም በትግራይ ክልል የሚኖረው ዐማራ የመመረጥ መብት የለውም፡፡ ዐማራው በብሔሩና ቋንቋው ተለይቶ በቀጥታና በነፃነት ተወካዮቹን አይመርጥም፡፡ በነፃነት የሚመርጣቸው ተወካዮች የሉትም፤ በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደርም አይሳተፍም፡፡ ይኽም እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን ከማምጣት ይልቅ ጥላቻንና ተቃውሞን ያስከትላል፡፡

መዝሙሩ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የኢትዮጵያን መንግሥት በሽምቅ ይወጋ በነበረበት ጊዜ "በታጋይ ኢያሱ በርሄ በ1978 ዓ. ም. የተደረሰ" ነው (መለይ፣ 2005፤81)፡፡ መዝሙሩ በተደረሰበት ጊዜ ለቅስቀሳ አገልግሎት እንደዋለ ያታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ከሥልጣን ከተወገደ በኋላም መዝሙሩ አገልግሎት መስጠቱ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ጠዋት የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር ዓርማ የነበረው የክልሉ ሰንደቅ ዓላማ በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጠዋት ሲሰቀልና በክልሉ አንዳንድ ዝግጅቶች ሲከናወኑ ይዘመራል፡፡ ቀጥለን በክልሉ በመዝሙሩ የተንጸባርቀውን ይዘት እንመለከታለን፡፡

### 3) በትግሉ ዘመን የተደረሰው የትግራይ መዝሙር ይዘት ትንተና

የትግራይ ክልል መዝሙር ምን እንደሚያንጸባርቅ በክልሉ ሕገ መንግሥት ከመደንገጉ በፊት መዝሙሩ በትምህርት ቤቶችና በክልሉ ፖለቲካዊ ዝግጅቶች ላይ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ይኽም በክልሉ መዝሙር የተንጸባረቀው ይዘት በክልሉ ሕገ መንግሥት ከደነገገው ጋር ላለመጣጣሙ ምክንያት ነው፡፡ መዝሙሩ በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገውን መሠረት አድርጎ፣ በወጣ መመሪያ ባለሙያ የግጥም ሥራውን በማቅረብ ተገምግሞ የተመረጠ አይደለም፡፡ ይኽ ባልኾነበት የክልሉ መዝሙር በሕገ መንግሥት ከተደነገገው ጋራ መጣጣሙን፣ ወይም አለመጣጣሙ መመርምር ተገቢ አይደለም፡፡ ይኹን እንጂ መዝሙሩ የሚያንጸባርቀውን ይዘት በመመርመር ክልላዊ ማንነትንና ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር በኩል ያለውን ሚና ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ምርመራችንም <u>በመምርሒ ስርዓተ ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን</u>

(መዳለዊ) (1995፤ X)[8] በትግርኛ የተጻፈውን በማስቀደምና የአማርኛውን ትርጉም በማስከተል እንጀምራለን፡፡ በይዘቱ ላይ ትኩረት ያደረገው ምርመራችን የአማርኛውን ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ትግርኛውን መዝሙር በመጥቀስ ትርጉሙን መሠረት በማድረግ እንመረምራለን፡፡

መስመር'ዩ ሓይልና

ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ
ፍፁም ወይከ የለን
መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና
ወይከ ኣይንምብርከኽን

ሃሩር ፀሓይ ነዳድ ህቦብላ ማይ በረድ
ማይ ማይ ትበል ነብሲ ኣብ ጀቖጀቖ ንረግረግ
ደንጎላ ንትርኣስ በዓቲ ይኹን ቤትና
ለይትን ቀትርን ጉዕዞ ንድከም ይጥመየና፡፡

መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ወይከ ኣይንሰዓርን
መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ወይከ ኣይንሰዓርን

ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ
ፍፁም ወይከ የለን

መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና
ወይከ ኣይንብርከኽን

ንከቡብ በዛብእ መሬት ትፅበበና
ኣብ ስጋና ይቀርቀር ኣስናን ፀላእትና
ስጋና ንኣሞራ ደምና ውሕጅ ይኹን
ኣዕፅምትና ይድቀቕ ሕሩጭ ኾይኑ ይበተን

[8]መለይ በ2005 ዓ. ም. ስለ ትግራይ የትጥቅ ትግል ባሳተሙት መጽሐፍ መዝሙሩን አሳትመውታል፡፡ ያሳተሙትም ትግርኛውን ከዐማርኛ ትርጉሙ ጋር ነው፡፡ በመለይ የታተመው መዝሙር በመምርሒ ስርዓት ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን (መዳለዊ) (1995) ከታተመው መጠነኛ ልዩነት ይስተዋልበታል፡፡ ልዩነቱም በቃላት አጠቃቀም፣ በሥንኝ አደራደር በአዝማች አጠቃቀም ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በመለይ የመዝሙሩ ሦስተኛ ሥንኝ የመጨረሻው ቃል “አይንሳዓርን/ከቶ አንሸነፍም” ሲባል በመምርሒ ስርዓተ ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን (መዳለዊ) ግን “ኣይንምብርከኽን/ከቶ አንሸነፍም [አንምበረከክም]” ተብሏል፡፡ እንደዚኹም በመለይ በተመዘገበው ከመጨረሻው ስድስተኛው ሥንኝ “ናይ ሶቪየት መርዛም ጋዝ ፋሽሽታዊ ንዳድ” ተብሎ የተመዘገበው በዚኸኛው “ናይ መድሓርሓርቲ ጋዝ ፋሽሽታዊ ነዳድ” በሚል ተመዝግቧል፡፡ በመለይ የመጨረሻውን ሥንኝ “ተዓወቲ ኢና (3)” ሲሉት ይኽ ጥናት በምንጭነት የተጠቀመበት ደግሞ “ክባታት ፀላኢ ክንፍንፅሖ ኢና (2)” በማለት መዝግቦታል፡፡ በተጨማሪም በመምርሒ ስርዓተ ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን (መዳለዊ) የመዝሙሩ የመጀመሪያዎቹ አራት ሥንኞች በአዝማችነት ሦስት ጊዜ ተደግመው ሲመዘገብ በመለይ በአዝማችነት ተደጋግመው አልተመዘገቡም፡፡

*መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ከባታት ፀላኢ ክንፍንፅሖ ኢና (2)*
*ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ*
*ፍፁም ወይከ የለን*
*መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና*
*ወይከ ኣይንብርከኽን*

*ናይ መድሓርሓርቲ ጋዝ ፋሽሽታዊ ነዳድ*
*ሚልዮን ቁምቡላታት ኣብ ቅድሜና ይነጎድ*
*መስዋእትን መቑሰልትን ከሳራታት ንኸፈል*
*ዝኸፍአ መከራ ውዲታት ይፍተልተል፡፡*

*መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ከባታት ፀላኢ ክንፍንፅሖ ኢና (2)*

የመዝሙሩ ርእስ "መስመራችን ኀይላችን" የሚል ነው፡፡ የመዝሙሩ የዐማርኛ ትርጉም ቀጥሎ የቀረበው ነው፡፡

*'ማንወጣው ተራራ 'ማንሻገረው ወንዝ*
*ፍጹም የትም የለም!*
*መስመራችን ኀይላችን ሕዝብ ነው ኀይላችን ከቶ አንሸነፍም!*

*የፀሐዩዋ ንዳድ የበረዶ ወጀብ ይዝነብ ከላያችን*
*በጥም እንቃጠል ረግረግ ይያዘን*
*ደንጊያን እንንተራስ ዋሻ ቤት ይኹነን*
*በሌት ተቀን ጉዞ እንድከም ይራበን፡፡*

*መስመራችን ኀይላችን ሕዝብ ነው ኀይላችን ከቶ አንሸነፍም!*
*መስመራችን ኀይላችን ሕዝብ ነው ኀይላችን ከቶ አንሸነፍም!*

*'ማንወጣው ተራራ 'ማንሻገረው ወንዝ*
*ፍጹም የትም የለም!*
*ዓላማ ግባችን ሕዝብ ነው ኀይላችን ከቶ አንሸነፍም!*

*በጅቦች ተከበን መውጫ መግቢያ እንጣ*
*የጠላታችን ጥርስ ከሥጋችን ይግባ እንደሾኽ ጋሬጣ*
*ሥጋችን ላሞራ ደማችን ወንዝ ይኹን*
*ዐጥንታችን ይድቀቅ በነፋስ ይበተን*
*መስመር ነው ኀይላችን የጠላት ከበባን መኻሉን ሰንጥቀን አይቀር*
*ማለፋችን! (2)*

*'ማንወጣው ተራራ 'ማንሻገረው ወንዝ*
*ፍጹም የትም የለም!*
*መስመራችን ኀይላችን ሕዝብ ነው ኀይላችን ከቶ አንበረከክም!*

የአድሃሪያን ጋዝ ፋሺስታዊ ንዳድ ሺ ተሚልዮን ፈንጂ ይፈንዳ ከኛ ፊት

እንክፈል ኪሣራ፡- ሞት ቁስለትእንግልት
የከፋ መከራ ሤራም ይጥፋ ይሙት
መስመር ነው ኀይላችን የጠላት ከበባን መኻሉን ሰንጥቀን አይቀር
ማለፋችን! (2)

"መስመራችን ኀይላችን" የሚለው የመዝሙሩ ርእስ የሚገልጸው የፖለቲካ ድርጅቱ ሲመሠረት አሳካዋለኹ ብሎ ያቀደውን ወይም ያለመውንና የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ዓላማም "የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፔርያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንዑስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ነው፡፡ ስለዚኽም የአብዮታዊዉ ትግል ዓላማ ከባላባታዊ ሥርዓትና ከኢምፔርያሊዝም ነጻ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ይሆናል፡፡"[9] (የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፣ 1968፤ 18) በተጠቀሰው የድርጅቱ መግለጫ እንደተገለጸው በትግራይ ሕዝብ ላይ ብሔራዊ ጭቆና የሚፈጽሙትና ለኋላቀርነትም የዳረጉት ሦስቱ ጣምራ ጠላቶቹ፡- 1ኛ አማራ፣ 2ኛ የጥገና ለውጥ የሚያራምደው የንዑስ ከበርቴ ቡድን እና 3ኛ ኢምፔሪያሊዝም ናቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የትግራይ ሕዝብ ለዐማራ ብሔራዊ ጭቆና የተጋለጠው ከዐፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ[10] ነው፡፡ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ የትግራይ ሕዝብ "በሸዋ አማራ የመሳፍንት ቡድንና ተከታዮቹ" ሥር በመውደቁ ነጻነቱ ተገፈፈ፤ አንድነቱ ተናጋ፤ ለድንቁርና፣ ለበሽታ፣ ለረሃብና ለስደት ተዳረገ ብሎ ማመን የተጠቀሱት ችግሮች በዐፄ ዮሐንስ የሥልጣን ዘመን በትግራይ ሕዝብ ላይ ላለመፈጸማቸው መከራከሪያ አይኾንም፡፡ ዐፄ ዮሐንስ የትግራይን ሕዝብ ከድንቁርና ለማላቀቅ፣ ከበሽታ ለመከላከል፣ ከረሃብ ለመታደግና ከመፈናቀል ለማዳን የሚያስችል ፖሊሲ አልነበራቸውም፡፡ በኤርትራ፣ በወሎ፣ በጎንደር፣ በጎጃምና በሸዋ ሲንቀሳቀሱ ከትግራይ ያስከተሉት ሠራዊታቸው በኼደበት ቦታ ነዋሪዎች ላይ በደል አልፈጸመም ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም፡፡ በታሪክ እንደሚታወቀው በወሎ የእስልምና እምነት ተከታዮችና በጎጃም ሕዝብ ላይ ያደረሱትን በደል ወደ ጎን በመግፋት "ጥፋት ያለው በሸዋ መሳፍንት ነው" ብሎ ማለት ትክክለኛውን የትግል መስመር አያመለክትም፡፡ "ዐፄ ምኒልክና ከእሳቸው በኋላ ወደ ሥልጣን የመጡት የሸዋ ዐማራ ስለኾኑ ሊገዙን፣ ሊመሩን አይገባም" ከማለት ያለፈ በታሪክ የሚጠቀስ በተለይ በትግራይ ሕዝብ

---

[9] ይኽ አቋም በድርጅቱ ውዝግብ ማስከተሉን በመጨረሻም የትግራይን ሪፐብሊክ መመሥረት የሚለው ሐሳብ እንዲቀር መደረጉን ገብሩ (2007፤ 40) እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ "አመራሩ ለትግራይ ጥያቄ መፍትሔው የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ማቋቋም ነው ያለውን፣ አብዛኛው ታጋይ አልተቀበለውም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በአመራሩ የተፈጠረ ልዩነት ስለመኖሩ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ መርሐ ግብሩ ከታጋዩ ባጋጠመው መጠነኛ ተቃውሞ የተነሣ፣ ከስድስት ወር በኋላ፣ የትግራይ አብዮት ዓላማ "የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ ማቋቋም ይሆናል" የሚለው አንቀጽ እንዲወጣ ተደረገ፡፡"

[10] በትግራይ ሕዝብ ላይ በደል ይደርስ የነበረው ከዐፄ ዮሐንስ የሥልጣን ዘመን ቀደም ብሎ እንደነበር የሚገልጹ አሉ፡፡ ሙሉጌታ (2002) እንደሚሉት የዐማራው የገዢ መደብ በትግራይ ሕዝብ ላይ በደል ይፈጽም የነበረው ከብዙ ዘመን ጀምሮ ነው፡፡ በ15ኛው ክፍለ ዘመን በሸዋ ነግሠው የነበሩት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በሃይማኖት ሰበብ በትግራውያን ላይ በደል ፈጸሟል፡፡ በዘመነ መሳፍንት መጨረሻ ላይ ከሰሜን እስከ ኤርትራ ይገዙ የነበሩት ደጃዝማች ውቤ በትግራይ ሕዝብ ላይ የከፋ ድርጊት ማድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡ እንደ ሙሉጌታ አገላለጽ ከዐፄ ዮሐንስ በኋላ የሸዋ የዐማራ መሳፍንት በትግራይ ላይ የሚፈጽሙት በደል ካለፉት ነገሥታት ሲያያዝ የመጣ ነው፡፡

ላይ የተፈጸመ በደል መጥቀስ አይቻልም፡፡ ከኹሉም በላይ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት የካቲት 11 ቀን 1967 ሲመሠረት "የሸዋ ዐማራ መሳፍንት ቡድንና ተከታዮቹ" የተባሉት መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ. ም. ከሥልጣን ተወግደው በወታደራዊ መኮንኖች ተተክተዋል፡፡ በትግራይ ሕዝብ ላይ ብሔራዊ ጭቆና የሚያደርስ በሌለበት እንደ አለ መቁጠር የትግል መሥመር ጥራትን አያስረዳም፡፡

ንዑስ ከበርቴያዊ የጥገና ለውጥ አራማጅ ተብሎ በየትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት በጠላትነት የተፈረጀው፣ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ. ም. ሥልጣን የያዘው የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት ነው፡፡ በጥገና ለውጡም ንኡስ ከበርቴያዊው የፋሽስት መንግሥት ከዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመተባበር  በኢትዮጵያ ሰፍኖ የቆየውን የብሔሮች ጭቆና በማባባስ እንዲራዘም ማድረጉን የፖለቲካ ድርጅቱ ያምናል፡፡ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት "ፋሽስታዊ ጠባዩን ለመሸፈን ሕዝቡን አታሎ የሕዝቡን ትግል ለማደናቀፍ ህብረተሰባዊነት[ን] መመሪያው አስመስሎ 'ህብረተሰባዊ' አዋጆች የመሬት ይዞታንና ትርፍ ቤቶችን በሚመለከት ዐዋጅ አወጣ፡፡ ይህ[ን] ያልንበት ምክንያት አዋጆች ሥራ ላይ ለማዋል በቅድሚያ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች በመኖራቸውና የአዋጁ መንፈስ አብዮታዊ መንገድ የተከተለ ሳይሆን የሕዝቡን ታቃውሞና የራሱ[ን] የኢኮኖሚ ውድቀት ለመወጣት የተጠነሰሰ ፖለቲካዊ ሴራ በመሆኑ ነው፡፡" (የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፣ 1968፤ 4) በማለት ጥገናዊ ለውጥ ያለበትን ምክንያት ገልጿል፡፡ "ፋሽስታዊው ወታደራዊ መንግሥት" የሚያራምደውን ጥገናዊ ለውጥ ለመታገል የትግራይ ብሔር ነጻነት የሚገኘው በትጥቅ ትግል ነው ብሎ በማመን የትጥቅ ትግል ጀመረ፡፡ ይኸ መስመር ሥልጣን ላይ የነበረውን ወታደራዊ መንግሥት ይቃወሙ የነበሩ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ይከተሉት ስለነበር የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅትን የተለየ የትግል መስመር እንደ አራመደ አያስቆጥረውም፡፡

የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት የትግል ዓላማ ዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን መታገል ነው፡፡ ዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን የሚታገለውም ያልበለፀጉ ሀገሮችን ሕዝቦች በየሀገሩ ካሉት አድሃሪያን ጋር በመተባበር እንደሚበዘብዘው ኹሉ ኢትዮጵያንም የጥገና ለውጥ ከሚያካኺደው ፋሽስታዊ ንዑስ ከበርቴ ጋር በመተባበር ይበዘብዛል ብሎ በማመን ነው፡፡ ይኸ የድርጅቱ ዓላማ በጊዜው የኢትዮጵያ መንግሥት ከነበረው የውጭ ግንኙነት አንጻር ሲመረመር ጥያቄ የሚያስነሣ ነው፡፡ በጊዜው የኢትዮጵያ መንግሥት ግንኙነት በሶቭየት ኅብረት ይመራ ከነበረው የምሥራቁ ጎራ ጋር ነበር፡፡ ይኽም በምዕራባውያን ከሚመራው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጎራ ውጪ እንደነበር ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት  ኢትዮጵያን የመራ ከነበረው ንዑስ ከበርቴ መንንግሥት ጋር ግንኙነት የነበረውን የሲቪየት ኅብረት እንደ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ይቆጥራል ማለት ነው፡፡ የፖለቲካ ድርጅቱ ማርክሲዝምን የሚያራምደው ከየትኛው ትክክለኛ ማርክሲስት አራማጅ ሀገር ጋር በመተባበር ነው?

የፖለቲካ ድርጅቱ ትግሉን የሚያካኺደው በማርክሳዊ-ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም በመመራት መኾኑን እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> ጭቆናውና ብዝበዛው ሊጠፋ የሚችለው የላብ አደሮችና የድሃ ገበሬዎች መደራጀት፣ ተደራጅተውም ወዝ አደሩ የግንባር ቀደምነት ታሪካዊ ተልእኮውን በመያዝ የፖለቲካ ትግሉን አፋፍሞ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማካሄድ ብቻ ነው፡፡ ወዝ አደሩንና ድሃ ገበሬውን ለማደራጀት በቅድሚያ ማርክሳዊ-ሌሊናዊ የሆነ የፖለቲካ ማሕበር ማቋቋም የግድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የፖለቲካ ማሕር በመላው ኢትዮጵያ የሚደረገውን የፖለቲካ ትግል በመምራት (ብሔራዊ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ካሉት ብሔሮች በስተቀር) በአሁኑ ጊዜ የትጥቅ ትግል በማድረግ ላይ ካሉት ጭቁን ብሔሮች ትግል ጋር በመተባበር ድልን አግኝቶ መደባዊ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና ለማጥፋት የዲሞክራሲና የሕብረተሰባዊነት መሠረት ሲጥል ብቻ መሆኑን በመረዳት

በጥቅሱ እንደተመለከተው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በመሸጋገሪያነት በመጠቀም ኅብረተሰባዊነትን መገንባት የሚለው በጊዜው ሥልጣን ላይ በነበረው የኢትዮጵያ መንግሥትም ይራመድ የነበረ ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡  ስለጭቁን ብሔረሰቦች የተገለጸው የፖለቲካ ድርጅቱ ከጥንስሱ ምን ሐሳብ ያራምድ እንደ ነበር ያስረዳል፡፡ ጭቁን ብሔረሰብ አለ ማለትም ጨቋኝ ብሔረሰብ አለ ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኽ ዓይነቱ አመለካከት ከፍተኛ ተቃውሞን እንደሚያስከትልና በሀገራችን ችግርም እንደ አስከተለ ካለፍንባቸው የኢሕአዴግ የሥልጣን ዓመታት እንረዳለን፡፡ የፖለቲካ መስመሩም  ትክክል ተደርጎ ሊቆጠር አይችልም፡፡

መዝሙሩ የተነገረው "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካቺ ተውላጠ ስም ነው፡፡ "እኛ" የሚለው የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ነው፡፡ በመዝሙሩ "ሕዝባችን ኃይላችን" በማለት ተደጋግሞ የተጠራው ደግሞ የቡድኑ አባላትንና ደጋፊዎችን ነው፡፡ "ሕዝባችን" የሚለው የእኛ ሕዝብ ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኽም፣ አንድም፣ የሕዝቡ ባለቤት የፖለቲካ ድርጅቱ ሕወሓት/ትሕነግ ነው፡፡ በባለቤትነቱም ሕዝቡን እንደፈለገ ያዘዋል፤ ያሰማረዋል፤ በአጭሩ የፖለቲካ ድርጅቱ አዛዥ፣ ሕዝቡ ደግሞ ታዛዥና ትእዛዝ ተቀባዪ ነው ማለት ነው፡፡ አንድም፣ ሕዝቡ የፖለቲካ ድርጅቱ አጋር ነው ማለት ነው፡፡ በአጋርነቱም የፖለቲካ ድርጅቱ ትብብር ሲጠይቀው ይተባበራል፤ ሕዝቡ የፖለቲካ ድርጅቱን ትእዛዝ የመቀበል ግዴታ ግን የለበትም ማለት ነው፡፡

በመዝሙሩ ውስጥ ተፈጥሮ በአሉታዊነትና በአዎንታዊነት ተገልጿል፡፡ በዝቶ የተነገረው መልክዐ ምድሩ በትግሉ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ ነው፡፡ ይኽውም፣ በትግል የተሰለፉት ታጋዮች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተራሮችና ወንዞች ፈተናዎች ኾነውባቸዋል፤ የፀሐዩ ሙቀት አቃጥሏቸዋል፤ የውኃ ጥም ላንቃቸውን አድርቆባቸዋል፤ በረዶ ደብድቧቸዋል፣ ከሰማይ በሚወርደው ዶፍ ብርድ አንዘፍዝፏቸዋል፤ ረግረግ ውጧቸዋል፡፡ ኾኖም፣ በትግሉ የተሰለፉት ታጋዮች ተፈጥሮ የሚያደርስባቸውን መሰናክል ተቋቁመዋል፡፡ ተራሮችን በመውጣትና በመውረድ፣ ወንዞችን በማቋረጥ የትግሉን ዓላማ እንደሚያሳኩ ያላቸውን እምነት መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ የተፈጥሮ ገጽታዎች የሚያደርሱባቸውን ችግሮች ተቋቁመው ዓላማቸውን ለማሳካት መቁረጣቸውንና ከሚያደርጉት ጉዞ አለመገታታቸውን  መዝሙሩ ያስረዳል፡፡ ..

በተለያዩ ቦታዎች ከሚገኙ የትግሉ አጋሮች ጋራ ለመገናኘት፣ ሕዝብን ለማደራጀት፣ "ጠላት" በሚሉት ላይ ጥቃት ለመሰንዘር፣ ከ"ጠላት" ጥቃት ለመሸሽ ወዘተርፈ ሌሊት በጨለማ፣ ቀን በብርሃን እንቅስቃሴ ማድረግና መጓዝ ትግሉ የሚጠይቀው ተግባር ነው፡፡ የተሟላ ስንቅ ሳይኖር ሌት ተቀን በሚደረግ ረጅምና የማያቋርጥ ጉዞ መራብ፣ መጠማት የትግሉ ፈተና ነው፡፡ ይኸን ዐይነት የትግል ገጠመኝ "በሌት ተቀን ጉዞ እንድከም ይራብን" የሚለው ሥንኝ ይገልጻል፡፡

ትግሉ ሳይጎለብት ራስን ከአውሬ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል መሣሪያ ሳይያዝ በተናጠልና ሰው በማይኖርበት አካባቢ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ ሌሊት በጨለማ ወይም በጨረቃ በተናጠል በሚደረግ ጉዞ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ የዱር አውሬዎች ያጋጥማሉ፡፡ ጥቃት ከሚያደርሱት የዱር አውሬዎች መካከል በመዝሙሩ የተጠቀሰው ጅብ አንዱ ነው፡፡ ታጋዮች በጅቦች ከበባ መግቢያ መውጫ ቢያጡም ዓላማቸው ግብ እንዲመታ ከሚያደርጉት ጉዞ ወይም የትግል እንቅስቃሴ ወደ ኋላ እንደማይሉ "በጅቦች ተከበን፣ መውጪያ መግቢያ እንጣ" የሚለው ሥንኝ ያስረዳል፡፡

በመዝሙሩ እንደ ተገለጸው ተፈጥሮ የትግል መሰናክል ብቻ ሳይኾን አጋርም ነው፡፡ "ድንጊያን ተንተርሰን፣ ዋሻ ቤት ይሁነን" በሚለው ሥንኝ እንደተገለጸው፣ ምቹ ትራስ በማይገኝበት የትግል ቦታ ድንጋይን መንተራስ፤ መጠለያ በሌለበት የተፈጥሮ ዋሻን እንደ ቤት በመጠቀም ራስን ከብርድ፣ ከዝናብ፣ ከጠላት እይታ መሰወር የተለመደ የታጋዮቹ ተግባር እንደነበር ያስረዳል፡፡

መዝሙሩ "ጠላት" ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት በመዘርዘር ታጋዮቹ ዓላማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ጉዞ እንደማይጉቱ ይገልጻል፡፡ "የጠላታችን ጥርስ ከሥጋችን ይግባ እንደሾህ ጋሬጣ" የሚለው ሥንኝ በትግሉ በተሳተፉት ላይ ከሚደርሱት ጥቃቶች አንዱ ነው፡፡ እንዲኽ ዐይነቱ ጥቃት እንዴት ሊደርስ ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ የተቃዋሚና የመንግሥት ኃይሎች በጦር መሣሪያ ከመጠቃቃት አልፈው የጨበጣ ውጊያ ይገጥማሉ፡፡ በጨበጣ ውጊያም፣ በተገኘው መሣሪያ ይጠቃቃሉ፡፡ በሳንጃ መሞሽላቀቅ (መወጋጋት)፣ በሰደፍ መመታታት፣ በድንጋይ መወጋገር፣ በቡጢ መናረት፣ በጥርስ መነካከስ፣ ተጠመዛዞ መጣጣል ወዘተርፈ ይፈጸማል፡፡ በተጠቀሰው ምክንያት በመዝሙሩ የተገለጸው በጥርስ ንክሻ የመጠቃት ያኸል እውነትነት አለው።

ትግሉን ወግነው በተሰለፉትና የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር በጠላትነት በፈረጃቸው የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት መካከል በሚደረገው የጦር መሣሪያ ትግል ሞትና ቁስለት ያጋጥማል፡፡ ደም እንደጎርፍ ይወርዳል፡፡ በመንግሥት ጥይት ለቆሰለ ርዳታ ለመስጠት፣ የሞተን የተቃዋሚ ወገን አስከሬን ለማንሣት፣ የማይቻልበት ኹኔታ ይፈጠራል፡፡ ከጠላት በደረሰ ጥቃት የሞተን "ታጋይ" አስከሬን ማንሣት በማይቻልበት ጊዜ የሟችን አስከሬን ሥጋውን አሞራና የዱር አውሬ ሊበላው ይችላል፡፡ በቀላል ወይም በጠንካራ የሕክምና ርዳታ መዳን ይችል የነበረ ቁስለኛ ደሙ ፈሶ ለሞት ይዳረጋል፡፡ ከዚኽም ሌላ፣ በ"ጠላት" ጥይት ወይም ፈንጂ ዐጥንቱ የሚከሰከስና የሚሰባበር ይኖራል፡፡ ይኸን ደርጊት መዝሙሩ፡-

*ሥጋችን ላሞራ፣ ደማችን ወንዝ ይኹን፣*
*ዐጥንታችን ይድቀቅ፣ በነፋስ ይበተን፡፡*

በማለት ይገልጸዋል፡፡

"ፋሺስቱ ደርግ" ከሰማይ በሚያዘንበው ቦንብ፣ በሚያፈነዳው ፈንጂ ሞት፣ ቁስለትና እንግልት በታጋዮቹ ላይ ቢደርስብንም በሽንፈት አንበረከክም፤ ዓላማችን ዳር ለማድረስ በጠራ መስመራችን እየተመራን ሕዝባችንን ከጎናችን አሰልፈን የጠላትን ከበባ ሰንጥቀን ወደ ዓለምነው ግብ እንደርሳለን የሚል መልእክት ተገለጿል፡፡

የትግራይ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የሚገልጸው በትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባርና በኢትዮጵያ መንግሥት ይመራ በነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት መካከል ጦርነት ይካኼድ በነበረበት ጊዜ ያጋጠመንና የሚያጋጥምነ ችግር ለመቋቋም ዝግጁ መኾንን፣ እንዲኹም፣ መሥዋዕትነት መክፈሉን ነው፡፡ የመዝሙሩ ዋና መልዕክትም "እኛ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር ታጋዮች በትግሉ ኺደት የሚያጋጥሙንን የተለያዩ መሰናክሎች አልፈን፣ ጠላታችንን አሸንፈን ዓላማችንን እናሳካለን" የሚል ነው፡፡ መዝሙሩ የትግሉን ከባድነትና አስቸጋሪነት በመግለጽ ማናቸውንም ዐይነት መሥዋዕትነት በመክፈል ትግሉን ዳር ለማድረስ ትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር ታጋዮች ያላቸውን ቁርጠኝነት ማስተማሩና መቀስቀሱ የታለመለትን ዓላማ ለማሳካት ይረዳል፡፡

ረጅሙን የትግል መዝሙር እያዜሙ ረጅም መንገድ መጓዝ ድካምን፣ ውኃ ጥምን፣ ረሀብን ለመርሳት ያግዛል፡፡ ታጋዮች አንድ ላይ ሰብሰብ ባሉበት ቦታ መዝሙሩን መዘመር፣ ያጋጠሙ አስቸጋሪ ኹኔታዎችን ለመርሳት፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችን ለመጋፈጥ ዝግጁ ለመኾን፣ የሞቱ የትግል አጋሮችን (ጓዶችን) በማሰብ መቆዘምን በመተው ለዓላማቸው የሕይወትና የአካል መሥዋዕትነት መክፈላቸውን እንዲያምኑ እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡ ወደፊት የሚያጋጥመን ከባድ የትግል ምዕራፍ ለማለፍ ወይም መሥዋዕትነት በመክፈል ትግሉን ወደፊት ለማራመድ ዝግጁ ለመኾን ብርታትን፣ ጥንካሬን፣ ትጋትን፣ ድፍረትን ይሰጣል፡፡ የመዝሙሩ መርዘም የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ እንጂ ችግር ሊኾን አይችልም፡፡ በጦርነት፣ በረሃብ፣ በውኃ ጥም፣ በረጅም የእግር ጉዞ፣ በእንቅልፍ ማጣት የዛለን አእምሮ ያነቃቃል፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣን ከመልቀቁ፣ ክልሉ ከመቋቋሙና ሕገ መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት የፖለቲካ ድርጅቱን አባላት ለመቀስቀስ፣ ለማትጋት፣ ለማበርታት፣ ለመሥዋዕትነት እንዲዘጋጁ አገልግሏል፡፡ የዚኽ መዝሙር ፋይዳው ለቅስቀሳ መጥቀሙ ነበር፡፡ ከዚያ አልፎ ግን የክልል መንግሥት መዝሙር ለመኾን በቅርጽና በይዘት ሊለወጥ ይገባው ነበር፡፡ አጭር፣ የክልሉና የሀገሪቱን ኹኔታ፣ የወደፊት አንድነትን፣ ዕድገትን ወዘተ. ሰፋ ያለ ሐሳብን ማካተት ይቻል ነበር፡፡

በገጠር ይደረግ የነበረው የትጥቅ ትግል አብቅቶ ሥልጣን ከተያዘ በኋላ መዝሙሩ በየትምህርት ቤቶች እንዲዘመር ማድረግ የሚዘምሩትን ተማሪዎች ለትግል፣ ለመሥዋዕትነት መጋበዝ ነው፡፡ ከዚኽም በላይ በክልሉ ሕገ መንግሥት መዝሙሩ እንዲያንጸባርቅ የተደነገጉትን ይዘቶች አልገለጸም፡፡ ይኹን እንጂ የተሻሻለው የትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት በ1994 ዓ. ም. ሲጸድቅ የተጠቀሰው መዝሙር በክልሉ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መዝሙሩ

የሚያንጸባርቃቸውን ይዘቶች ይደንገግ እንጂ በትግራይ ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ይዘመር የነበረውና ዛሬም በክልሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚዘመረው መዝሙር ይዘት ጋራ አይጣጣም። በመኾኑም፣ መዝሙሩ ወቅታዊ በነበረው ትግል ላይ የሚያተኩር በመኾኑ ወጣቶችን ስለሰላም የሚያስተምር አይደለም። ከዚኽ ይልቅ ጦርነትን፣ መሥዋዕትነትን፣ ትግልን፣ ጽናትን መስበኩ በጊዜው በፖለቲክ ድርጅት የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር ይሰበክ የነበረውን “የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ድህነትና ኋላቀርነት ነው” የሚለውን የሚቃረን ነበር። በተጨማሪም፣ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የሽምቅ ውጊያ ያካኺድ በነበረበት ጊዜ ለቅስቀሳ ያገለግል የነበረው መዝሙር በይዘቱ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የማያተኩር፣ በቅርጹም ረጅም በመኾኑ በትምህርት ቤት መዝሙርነት እንዲያገለግል መደረጉ ተገቢ አይደለም።

## 4) ማጠቃለያ

በ1994 ዓ. ም. በተሻሻለው የትግራይ ክልል ሕገ መንግሥት የትግራይ ክልል መዝሙር የክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ የክልሉን ሕዝብ ባህል፣ የትግል ታሪክ፣ አንድነትና ብሩህ ተስፋ ማንፀባረቅ እንደሚገባው ተደንግጓል። እነዚኽን የክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ክልሉን በብቸኝነት የሚመራው የፖለቲካ ድርጅት በሚያስተዳድረው ሕዝብ ማስረጽ የሚፈልጋቸው ናቸው። ይኹን እንጂ፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን ኹሉንም መዝሙሩ እንዲንፀባርቁ ማድረግ ይቻላል ብሎ ለመቀበልም፣ ለማሰብም ያስቸግራል። የክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ማንፀባረቅ በሚለው የተጠሩትን ፍትሕን ማስፈን፣ የክልሉን ሕዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበር፣ የክልሉን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ማፋጠን፣ የብሔር-ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማክበር፣ በክልሉ ዘላቂ ሰላም ማስፈን፣ እኩልነትንና አንድነትን ማረጋገጥ የሚሉትን ዘርዝሮ በመዝሙሩ እንዲንፀባረቁ ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በተጨማሪ መዝሙሩ የፖለቲካ ድርጅቱን/የሕዝቡን የትግል ታሪክ፣ የትግራይ ብሔር፣ የኩናማና የኢሮብ ብሔረሰቦች ሊፈጽሙ የሚገባቸውንና ወደፊት ሊደርሱበት የሚገባቸውን ወይም የሚበጃቸውን የወደፊት የጋራ ዕድላቸውንና የወደፊት ሕይወታቸው የተሻለ መኾኑን የሚያንፀባርቅ እንዲኾን መደንገጉ ብዙ ነገር በመዝሙሩ እንዲገለጽ መፈለግን ያስረዳል። ለክልሉ ሕዝብ የተሻለ ሕይወት መፈለግ፣ መከጀልና መጓጓት ዛሬ ባለው ነባራዊ ኹኔታ የነገውን የሕዝቦች ሕይወት ብሩህነት አስተማማኝ መኾኑን ይግለጽ እንጂ በአጭር ጊዜ መዘመር በሚገባው መዝሙር ብዙ ሐሳብ አጭቆ ማቅረብ ተገቢነት የለውም ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።”

በትግራይ ክልል መዝሙር ምን ምን መንጸባረቅ እንዳለበት በክልሉ ሕገ መንግሥት ቢደነገግም የሚዘመረው ግን በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን የሚያንፀባርቅ አይደለም። መዝሙሩ የክልሉን ሕዝብ “ከጭቆና፣ ከበደል፣ ከብዝበዛ ነጻ አወጣለኹ” ብሎ ይታገል የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ለቅስቀሳ ይገለገልበት የነበረ መዝሙር ነው። የፖለቲካ ድርጅቱ የትጥቅ ትግል ያካኺድ በነበረበት ጊዜ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው መዝሙር፣ ድርጅቱ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ. ም.

ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንባር መሥርቶ ሥልጣን ከያዘ በኋላም አገልግሎት መስጠቱ እንዲቀጥል ተደረገ። በኢትዮጵያ በተቋቋመው የሽግግር መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን ድርሻ የነበረው ትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት በኋላም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከፍተኛ የኀላፊነት ቦታዎችን ይዞ እስከ 2010 ዓ. ም. መጋቢት ወር ድረስ በቀጠለበት ጊዜም መዝሙሩ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ከዚኽ ጊዜም በኋላ የትግራይን ክልል እስከ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ. ም. ድረስ በብቸኝነት ሲመራ መዝሙሩ አገልግሎት ሰጥቷል። መዝመሩም የፖለቲካ ድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ለትግል የሚያነሣሣና ለመሥዋዕትነት እንዲዘጋጁ የሚቀሰቅስ ነው። የክልሉን ሥልጣን የያዘው መንግሥት መዝሙሩን እንዲዘመር የሚያደርገው ማንን ለመታገልና ሕዝቡን ከማን ነጻ ለማውጣት አስቦ እንደኾነ ግልጽ አይደለም።

ለትግል ማነሣሻ የተደረሰው መዝሙር ሰላምን፣ ዕድገትን፣ ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ መኖርን፣ የሕገ መንግሥቱን የበላይነት አያንፀባርቅም። በትግራይ ክልልም ኾነ በሌሎች ክልሎች አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል በተባለበት ጊዜም መዝሙሩ ለጦርነት የሚያነሣሣ ነው። ከዚኽም በላይ እንዴትና መቼ መዘመር እንዳለበት በሕግ አልተደነገገም፤ መመሪያምአልወጣለትም። በመኾኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርና የክልሉ መዝሙር በሚዘመርበት ቦታ (ለምሳሌ በትምህርት ቤቶች) ማንኛው ቀድሞ እንደሚዘመር በሕግ ባለመደንገጉ ወይም መመሪያ ባለመኖሩ የፈለጉትን በማስቀደም ይዘምራሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር ቀጥሎ የክልላቸውን መዝሙር ሲያዘምሩ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከዚኽ በተቃራኒው ያዘምራሉ።

ለክልሉ መዝሙር ያስፈልጋል ከተባለ የክልሉ ሕዝብ ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ አካል መኾን በትክክል የሚያንፀባርቅ፣ በሌሎች ክልሎች ከሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በእኩልነት መኖርን የሚያስተምርና ኢትዮጵያዊ ስሜትን የሚያኀለብት መኾን ይገባዋል።

## መረጃ ጽሑፎች


ህ.ወ.ሓ.ት [ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ]:: 1979:: *የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወደየት (ግምገማ)*:: (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)::

መለይ አማረ:: 2005:: *ብሶት የወለደው የትግራይ ህዝብ የትጥቅ ትግልና የህወሓት አመራር (1967-1981 ዓ. ም)*:: (የታተመበት ቦታ አልተገለጸም)፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

መምርሒ ስርዓተ ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን (መዳለዊ):: 1995:: *ትምህርቲ ኤስቴቲክሥን ጥንካረ አካልን መምርሒ ንመምህር ፲ᵉ ክፍሊ*:: መቐለ (ማተሚያቤቱ አልተገለጸም)::

ሙሉጌታ ደባልቀው:: 2002:: *ጋሳሀቲ ሠጊ፤ የህወሓት የትጥቅ ትግል ታሪክ (1967-83 ዓ. ም.)* :: (የታተመበት ቦታ አልተገለጸም)፤ Mega Printing PLC.

ሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት:: 1995:: ዐዋጅ ቁጥር *የተሻሻለው የሱማሌ ክልል ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ ማዋሉን ለማሳወቅ የወጣ ዐዋጅ ቁጥር* ፲፫ህ፲፱፻፺፬:: ጅጅጋ::

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቲ ትግራይ:: ትግራይ ክልል ሰንደቅ አላማ ለመወሰን የወጣ ዐዋጅ ቁጥር 2/1988:: *ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ::*

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቲ ትግራይ:: *ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ ዐዋጅ ቁጥር 45/1994* :: *ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ*:: 10ኛ ዓመት፣ ቁጥር 2፣ ሕዳር 6 1994፣

ብሔራዊ መዝሙር ዝግጅት ኮሚቴ:: "ለኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ማስታወሻ"፤ ሰኔ 2 ቀን 1984::

ተክለጻድቅ መኩሪያ:: 1982:: *ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት*:: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት

ትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት:: 1968:: "*መግለጫ* (ት. ህ. ነ. አ. ድ) የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት" (*የመጀመሪያ* እትም):: at: https: www. Satenaw.com/https-www satenaw-com-wp-content-uploads 2017, accessed on 5 May 2019.

ቹቹ አለባቸው:: 2011:: *ዳገት ያበረታው የአማራው ፍኖት*:: (አርታኢ ገዛኸኝ ፀጋው) ባሕር ዳር፤ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)::

አረጋዊ በርሔ::2013:: *የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ፖለቲካዊ ታሪክ (1967-1983)፣ አመፅ ርዕዮተ ዓለምና መሰባሰብ በኢትዮጵያ*:: (ሁለተኛ ዕትም) አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር::

ኢትዮጵያ *ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ* የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት::" የድሬ ዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996:: *ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ::*

ኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ፣ "የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር"፣ *ነጋሪት ጋዜጣ*፡ አምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ሐምሌ 15 ቀን 1983::

ኢትዮጵያ የሽግግር *መንግሥት* የተወካዮች ምክር ቤት 70ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ግንቦት 3 ቀን 1985::

ኢትዮጵያ የሽግግር *መንግሥት* የተወካዮች ምክር ቤት 33ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ጥር 28 እና 30፣ 1984::

ኢትዮጵያ የሽግግር *መንግሥት* ነጋሪት ጋዜጣ፣ "ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1984::" ኢትዮጵያ የሽግግር *መንግሥት* ነጋሪት ጋዜጣ::

ኢትዮጵያ የሽግግር *መንግሥት* የተወካዮች ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ፣ አዋጅ ቁጥር 7/1984

ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤ *የኢትዮጵያ የሽሽግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ*::

ኢትዮጵያ *ፌዴራላዊ* ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት:: የኢትዮጵያ *ፌዴራላዊ* ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987:: *ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ* ::

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር አዋጅ ቁጥር 673/2002፡፡ *ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ፡፡*

ያሬድ ጥበቡ (ጀበሳ)፡፡ 2010፡፡ *ወጠቼ አልወጣሁም፤ የሩብ ክፍለ ዘመን ዋይታዎች (1983- 2008)*፡፡ (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤቱ አልተገለጹም)፡፡

ጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ 1995፡፡ *የተሻሻለው የ1995 ዓ. ም. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ- መንግሥት ዐዋጅ ቁጥር 27/1995*፡፡ ጋምቤላ፡፡

ገብሩ አሥራት፡፡ 2007፡፡ *ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ*፡ (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤቱ አልተገለጹም)፡፡

ጌታቸው ኃይሌ፡፡ 1995፡፡ *የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፤ ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች*፡ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)፡፡

Aregawi Berhe. 2008. *A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991)፡ Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia*. Amsterdam: VRIJE UNIVERSITEIT.

Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority.1998. *The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Tigray Region Volume II Analytical Report.* Addis Ababa.

Shiferaw Bekele. “The State in Zamana Masafent (1786-1855). 1990. An Essay in Reinterpreta- tion”; *KASA and KASA፡ Papers on the Lives, Times and Images of Tewdros II and Yohannes IV (1855-1889.* (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhurst and Shiferaw Bekele) Addis Ababa University: Institute of Ethiopiaian, PP.25-68.

<u>**አባሪ፡- ሕዝብ/ሕዝቦች ቃላት ዐውዳዊ አገልግሎት የተሰጠ ማብራሪያ**</u>

ሕዝብየሚለው ቃል በክልሉ ሕገ መንግሥት በተጠቀሰበት ዐውድ የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች የወል መጠሪያ ነው፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 "በትግራይ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የትግራይ ብሄር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ ማገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የትግራይ ብሔራዊ ክልል <u>ህዝብ</u>" በማለት የተጠቀሱትን ብሔር-ብሔረሰቦች ዲሞክራሲያዊ መብቶች መዘርዘሩ የቃሉን ዐውዳዊ ፍቺ ያስረዳል፡፡ ቃሉ ክልል ከሚለው ቃል ጋር ተጣምሮ መነገሩም የክልሉን ብሔር-ብሔረሰቦች ማለት ለመኾኑ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ይኹን እንጂ ሕዝብ የሚለው ቃል በወል መጠሪያነቱ በወጥነት እንዲያገለግል አልተደረገም፡፡ ለምሳሌ፣ አንቀጽ 39 "የትግራይ ብሐራዊ ክልላዊ <u>ሕዝቦች</u> የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ ማገንጠል" በማለት ቃሉ በብዙ ቁጥር ተተክቷል (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ከዚኽም በላይ በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ሕዝብና ሕዝቦች በማለት የክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦች ተጠርተዋል፡፡ "እኛ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህዝቦች"፣ "የትግራይ ህዝብ"፣ "እኛ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የምንገኝ ህዝቦች" እና "የዚህ ክልል ህዝቦች" የሚሉት ሐረጎች በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ የሚነበቡ ናቸው፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች በማለት የተጠሩትን "ሕዝብ" እና "ሕዝቦች" በነጠላና በብዙ ቁጥር በማፈራረቅ የመጠቀሙ ምክንያት፣ አንድም፣ተገቢውን ትኩረት ባለማስጠት፣ ወይም ጥንቃቄ ባለማድረግ  ነው፡፡ አንድም፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞግራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የቃሉ አጠቃቀም ግልጽ አለመኾን የፈጠረው ችግር ወይም ስሕተቱ በትግራይ ክልል ሕገ መንግሥትም በመደገሙ ነው፡፡ ይኽ ዓይነቱ ስሕተት በኹሉም የክልል ሕገ መንግሥቶች እንደተፈጠረ በየሕገ መንግሥታቸው ማስተዋል ይቻላል፡፡ ብሔር ወይም ብሔረሰብ እንደኾኑ የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝብ ተብለው መጠራታቸውን ሊቀበሉ አይችሉም፡፡ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ (ምናልባትም ኢኮኖሚያዊ) ደረጃቸውን ዝቅ ያደረገባቸው አድርገው  ሊቆጥሩ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ስለ የትግራይ ብሐራዊ ክልል መዝሙር በተደነገገው "ከሌሎች የኢትዮጵያ <u>ህዝቦች</u>" በሚለው ሐረግ "ህዝቦች" የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካቹ ቃል የሚጠራው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ዐዋጅ ቁጥር 1/1987 መግቢያ እና በአንቀጽ 39 (1 - 5) ላይ "የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች" በማለት የተጠሩትን ነው፡፡ ለመጠሪያዎቹ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንዳቸውን ከሌላኛቸው ለመለየት የሚያስችል ድንጋጌ አልተሰጣቸውም፡፡በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 በአንቀጽ 39 (5) "በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" ማለት ከዚኽ ቀጥሎ የተገለጸውን ባሕርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣  የጋራ ወይም  የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና ባብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" የሚሉት መጠሪያዎች በመካከላቸው ምንም ልዩነት አልተነገረም፡፡ ከዚኽም በላይ ብሔርና ብሔረሰብ የሚሉት መጠሪያዎች የሰዎች ስብስብ መጠሪያ መኾናቸው ትክክል አይመስልም፡፡ ምክንያቱም፣ "ብሔር" ማለት ሀገር፣ መልከዓ-ምድር ማለት ሲኾን "ብሔረሰብ" ማለት ደግሞ ሰው የሚኖርበት ሀገር" ማለት ነው። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ  ሰዎች ማለት ከተፈለገ ግን "ሰብአብሔር" መባል ነበረበት። ይኹን እንጂ አብዛኞዎቹ ክልሎች በየሕገ መንግሥታቸው ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የሚሉትን መጠሪያዎች ለተለያዩ

ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የተሻሻለው የሱማሌ ክልል ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር “፲፰ሀ/፲፱፻፺፬” [፲፰/፲፱፻፺፬] አንቀጽ ፴፱ የሱማሌ ብሔር በማለት ተጠርቷል፡፡ የተሻሻለውን የጋምቤላ ክልል ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር “፳፯/፲፱፻፺፰” አንቀጽ ፵፯ የክልሉ መንግሥት አባላት የአኙዋ ብሔረሰብ፣ የኑዌር ብሔረሰብ፣ የማጃንግ ብሔረሰብ፣ የኦፖ ብሔረሰብና የኮሞ ብሔረሰብ መኾናቸው ተደንግጓል፡፡